ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ፈንታነሽ ጌቴ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጥናት

የካቲት 2015 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ
ፈንታነሽ ጌቴ

አማካሪ፡- ማንያለዉ አባተ (ዶ/ር)

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጥናት

የካቲት 2015 ዓ.ም
ጅማ ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

# ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር

ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በፈንታነሽ ጌቴ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ............................................. ፊርማ.................... ቀን...................

የውስጥ ፈታኝ.................................. ፊርማ.................... ቀን...................

የውጭ ፈታኝ..................................... ፊርማ.................. ቀን...................

## ምስጋና

በቅድሚያ ይህን ጥናት በፍቃዱ አስጀምሮ እንድጨርስ ለረዳኝ ልዑል እግዚያብሔር ከነ እናቱ ምስጋና ይግባው ። በመቀጠልም አባታዊ ምክርና ሙያዊ እገዛ በማድረግ ይህ ስራ ከግብ እንዲደርስ ለረዱኝ ለዶ/ር ማንያለው አባተ ምስጋናዬ ከፍያለ ነው። ከዋና አማካሪዬ በተጨማሪ ሞያዊ እገዛ ላደረጉልኝ ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። የምርምር ትምህርት በማስተማርና እውቀት በማስጨበጥ እንዴት እንደሚሰራ መሰረት ለሆኑኝ ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ምስጋናዬ ይድረሳቸው ። ከመንግስት በተጨማሪ የገንዘብ፣ የሀሳብ ድጋፍ በመስጠት እና ልጆቼን በመያዝ ላልተለየኝ ባለቤቴ ምስጋና ይግባው። ለሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እና ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። በመጨረሻም ለቤተሰቦቼና ለልጆቼ ምስጋና ይገባል።

**ማዉጫ** **ገጽ**

ምስጋና ........ I
አጠቃሎ ........ II
ምዕራፍአንድ ........ 1
መግቢያ
1.1.የጥና ቱዳራ ........ 1
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 5
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 5
1.4.1 ዐብይ ዓላማ ........ 5
1.4.2 ንኡሳን ዓላማዎች ........ 5
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 5
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 7
1.8 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ተግባራዊ ብያኔ ........ 7
ምዕራፍ ሁለት
ክለሳ ድርሳናት ........ 8
2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........ 8
2.1.1 የተነሳሽነት ምንነት ........ 8
2.1.2 በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተነሳሽነት ጠቀሜታዎች ወይም ሚና ........ 9
2.1.3 የተነሳሽነት ዓይነቶች ........ 11
2.1.3.1 ዉስጣዊ ተነሳሽነት ........ 11
2.1.3.2 ውጫዊ ተነሳሽነት ........ 13
2.1.4 የተነሳሽነት ተላውጦዎች ........ 15
2.1.5 የአንብቦ መረዳት ምንነት ........ 17
2.1.6 የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች እና ደረጃዎች ........ 18
2.1.6.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች ........ 18
2.1.6.2 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች ........ 20
2.1.7 የአንብቦ መረዳት መስፈርቶች ........ 21
2.1.8 የመማር ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ ........ 22

2.2 ፅንሰ ሀሳባዊ ማህቀፍ ........ 23
2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 24
ምዕራፍ ሶስት
የጥናቱ ንድፍ እና አካሄድ ........ 29
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 29
3.2 የጥናቱ አካላይ ........ 29
3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 29
3.3.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 29
3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 30
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 30
3.4.1. የጽሁፍ መጠይቅ ........ 31
3.4.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና ........ 31
3.5 የመረጃ አተናተን ........ 32
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ........ 33
4.1 ተጠኚዎቹ በሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ........ 33
4.2 የተጠኚዎቹ በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ........ 37
4.4 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 38
ምእራፍ አምስት
ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ ........ 40
5.1 ማጠቃለያ ........ 40
5.2 መደምደሚያ ........ 41
ዋቢዎች ........ 43
አባሪዎች
አባሪ አንድ ........ 47
አባሪሁለት ........ 56
አባሪሦስት፡ ........ 63

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1 ተጠኚዎቹ በሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ስላላቸው ውሁድ ተነሳሽነት ............33
ሰንጠረዥ 4.2 ተጠኚዎቹበሁለተኛ ቋንቋለመማር ስላላቸው ውስጣዊናውጫዊተነሳሽነት ...34
ሰንጠረዥ 4.3 የጥናቱተተኳሪዎችበሁለተኛቋንቋየመማርውስጣዊናውጫዊ........................35
ሰንጠረዥ 4.4 የተጠኚዎቹ አንብቦ የመረዳትፈተናውጤት..............................................36

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ የመማር ተነሣሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት መፈተሽ ነው። የጥናቱን አላማ ለማሳካትም ተዛምዷዊ የምርምር ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። ጥናቱ በአመቺ የንሞና ዘዴ በተመረጠ በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ነው።በተጨማሪም የ10ኛ ክፍልን በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ በመጠቀም የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ሆነዋል። የጥናቱ ተሳታፊዎችም በእኩል እድል ሰጪ የንሞና ዘዴ የተመረጡ 97 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። የመማር ተነሳሽነታቸው አማካይ ውጤት 3.027 ሆኖ ተመዝግቧል። የተማሪዎቹ የመማር ተነሣሽነት መደበኛ ልይይት0.36814 ሲሆን የእያንዳድ ተጠኚ ምላሽ አማካይ ውጤት ርቀቱ ጠባብና የማያዋዥቅ ሲሆን ተማሪዎች ከውስጣዊ ተነሣሽነት የበለጠ ለውጫዊ ተነሣሽነት ትኩረት የሰጡ ሲሆን ጉልህ ልዩነት ግን እንደሌለ በባድ ናሙና ፍተሻ ተረጋግጧል። ዉጤቱም 0.76 ሆኖ ተመዝገቧል። የተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታ በአማካይ ውጤታቸው ተሰልቷል። በተማሪዎች የመማር ተነሣሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ በእስታቲክስ፣ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ተሰልቷል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም የተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት(53.938) መሆኑ በናሙና ፍተሻ ተረጋግጧል። ነገር ግን ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለ ለማለት አያስደፍርም። በመማር ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት መካከልም አዉንታዊ ተዛምዶ አልታየም። ውጤቱም (r= -049 የ"P" ዋጋ 0.852 ወይም P > 0.5) በመሆኑ አሉታዊ ተዛምዶ መሆኑ ተረጋግጧል።*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሪጥያቄዎች አብይ እና ንዑሳን አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን እና የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ በቅደም ተከተል ተገልጿል፡፡

በጥናቱ ዳራ የጥናቱ ክፍተት ከአጥኚዎችና ከምሁራን ሀሳብ በመነሳት ተዳሷል ፡፡ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የአጥኚዋ የግል ገጠመኞች በምሁራንና በአጥኚዎቹ ንድፈ ሀሳብ መነሻነት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ መሪ ጥያቄዎች የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት አድርገው ፡ የጥናቱ ዋና አላማ አጠቃላይ ሲሆን በመሪ ጥያቄዎች አማካኝነት ንዑሳን አላማዎች ተነድፈዋል፤ የጥናቱ አስፈላጊነት በጥናቱ ሊገኙ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ጠቀሜታዎች ቀርበዋል፤ የጥናቱ ወሰን ከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከይዘትና ከተለዋዋጮች አንፃር የተገለፀ ሲሆን በመጨረሻም የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ ተቀምጧል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቀለ (2000) ቋንቋ ከመማር ተግባቦት አንፃር ሲታይ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ከመማር ይለያል፡፡ ይህም ሲባል የግለሰብን ማህበራዊ ማንነት ከሌሎች ማህበረሰብ ጋር ያለውን ተግባቦት በመከታተል እና አመለካከቱን በማስተካከል ከታለመው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና ማህበራዊ ባህሪ ጋር እራሱን የሚያስተማምንበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ግለሰቡ በቋንቋ ትምህርቱ ተነሳሽነት ሲኖረዉ ነው፡፡

ተስፋዬ (2014) ቋንቋ ከሰዎች አንደበት የሚፈልቅ ድምጻዊ መግባቢያ ሲሆን የህብረተሰብን የማህበራዊ ኑሮ መዋቅር በማዋቀር ውስጥ እርስበእርስ የሚያደርገውን ግንኙነት፣ የመተዳደሪያ ስርዓቱን ደንቡን፣ እምነቱን፣መሳሪያውን ና እውቀቱን የሚቀበልበትን ተቋምና ዘዴውን ሁሉ አካቶ የያዘ በመሆኑ ማንነትን በማሳየት እረገድ ትልቅ ሚና እንዳለዉ አሳይቷል፡፡

Bill(2000)ን በመጥቀስ ደግሞ የቋንቋ ትምህርትን በተነሳሽነት የሚማር ተማሪ በተማረው ትምህርት ዘርፍ ግንዛቤን፣ ትውስና አዕምሮአዊ ዕድገትን ያገኛል፡፡ ምክንያቱም ተነሳሽነት ያለው ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ላይ አወንታዊ አመለካከት ስለ ሚኖረው አንድን ድርጊት ለመፈፀም ይደፋፈራል፡፡ አዕምሮአዊ መንፈሳዊና አካላዊ ጥረት ያደርጋል፤ በዚህም የተነሳ ካለመው ግብ ይደርሳል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተማሪዎች የተነሳሽነት ሁኔታ አወንታዊና አሉታዊ አመለካከታቸውን የሚወሰን ሲሆን የመማር ማስተማሩን ሂደት ከግብ ለማድረስ

የተማሪዎችን ሁኔታ የምንለይበት ነው። ከዚህም አኳያ ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው በጨመረ ቁጥር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከፍ እንደሚል መሪነሽ (2004) ገልፃለች።

የመማር ተነሳሽነት ካሰቡት ግብ ለመድረስ እና ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት መሰረት መሆኑን Giirg (2016) ይጠቅሳል። በመሆኑም የተማሪዎችን የስነ ልቦና በሂደት ለመከታተል የበለጠ ውጤት እንዲያመጡ የምንሰራበት መሆኑንይገልጻል። Feldam (2004) ተነሳሽነት የሰዎችን የማሰብ ሀይል እና ጥንካሬ የምንለይበት መሆኑን ይገልጻል። Nuredin (2021) ተነሳሽነት ዋና የስራ ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚደረግ ክንውን መሆኑን በመግለጽ የመማር ማስተማር ስራውን ለማከናወን በተለይ የሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን ገልጿል።

Gass And Selnker(2008) ተነሳሽነት ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል። Mehadi And Jafer(2012) ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ምኞት፣ ፍላጎት እና ሐሳብ ለማወቅ እያስተማርን የምንረዳበት መሆኑን ገልጸዋል። Donory(2009) ተነሳሽነት የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝንባሌ እንዲሁም ችሎታ የምንለካበት አውቀንም አወዳድረን ደረጃቸውን የምንለካበት መንገድ መሆኑን ገልጸዋል። አያይዘውም የሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር የተማሪዎችን አስተሳሰብና ግላዊ ፍላጎት በመረዳት የመማር ማስተማር ሂደቱን አቅጣጫ የምናስተካክልበት መሆኑን አብራርቷል። Eshun And K.Duah(2011) ተነሳሽነት ችግሮችንና የተለያዩ ውጣውረዶችን ወደ አንድ የቆሙለት ምንጭ በማምጣት ወደ አንድ ቡድን ወይም መፍትሔ የሚደረግ ተፈጥሮአዊ ለውጥ ነው።

ከምሁራኑ ሐሳብ ለመረዳት እንደተቻለው ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋን የመማር ማስተማር ስራ ለማከናወን ተነሳሽነት መሰረት፣ ቁልፍጉዳይ፣ የተማሪዎችን ችሎታ፣ ግንዛቤ፣ አመለካከትና አስተሳሰብ ማወቅነው። በመሆኑም መምህሩ የተማሪዎቹን ሁኔታ በማወቅ የመማር ማስተማር አቅጣጫን በማስተካከል ለታሰበው ዓላማ ግብ መምታትና ለተማሪዎች ውጤት ተነሳሽነት ትልቁ ጉዳይ ነው። ተነሳሽነትን በተመለከተ በሀገር ውስጥ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል። ከነዚህም መካከል ዘሪቱ(2004) አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ መሪነሽ(2004) የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ አይታለች።

የመሪነሽ ጥናት የማንበብ ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለዉን ተዛምዶ የፈተሸች ሲሆን ያነሳችዉ ይዘት ተነሳሽነትንና የአንብቦ መረዳትን የያዘ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲመሳሰል ይህ ጥናት የመማር ተነሳሽነትን በመያዙ ከእሷ ጥናት ይለያል።

ዘሪቱ (2004) ደግሞ የመማር ተነሳሽነት በመያዙ ሲመሳሰል የእሷ ጥናት የትምህርት ዉጤት አጠቃላይ የሚፈትሽ ሲሆን ይህ ጥናት የመማር ተነሳሽነትን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመዱ ይለያል፡፡

የተስፋዬ ጥናትም የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ዉጤት ጋር በማዛመዱ ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ቢዛመድም አንብቦ መረዳትን አለማየቱ ይለያል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ተነሣሽነት የሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ጠቃሚ እና ዋና ጉዳይ መሆኑን በማመን በርካታ የሀገር ውስጥእና የውጭ ጥናቶች ጠቁመዋል፡፡ ለአንብቦ መረዳት ችሎታየተማሪዎች የመማር ተነሣሽነትአስፈላጊ እና ለአሰቡት ግብ መሳካት መሰረት ነው፡፡ እና ለአስቡት ግብ ለመድረስ መማር፣ ማንበብ እና ለማንበብ እና ለመማር ደግሞ ተነሳሽነት አስፈላጊ ነው፡፡

Cle` Ment and Ryan (2009) የሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተማሪዎች ተነሳሽነት ለከፍተኛ እውቀትና ውጤት እንደሚያበቃ ገልፀዋል፡፡ Nuredin (2021) አንድን አላማ ከግብ ለማድረስም ሆነ የስራ ሂደትን ለማከናወን ተነሳሽነት አስፈላጊ መሆኑን ሲገልፅ Gass And Selinker (2008) ደግሞ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ቁልፍ ጉዳይ ነው፤ ይላሉ፡፡ L knoll (2000) ደግሞ አንብቦ መረዳት የከበደንና የተወሳሰቡትንን ነገር ተምረን በማንበብ ወይም ከመምህራን የምንረዳበት ክሂል መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

Achiwa(2014) የተማሪዎችን ውጤት በመወሰን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ትልቅ ሚና እንዳለው አስረድቷል፡፡ አጥኚዋም የምሁራኑን ሀሳብ እንደ መነሻ በማድረግ እና የሌሎች አጥኒዎችን ፈር በመከተል የተማሪዎቹን የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመፈተሽ ተነሳስታለች፡፡ Phakiti(2006)፣Celcie-Murcia(1991) ማንበብን በተመለከተ ማብራሪያ ሲሰጡ በሁለኛ ቋንቋ ማንበብ ከመጀመሪያ ቋንቋ ማንበብ በበለጠ ውስብስብ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ተነሣሽነት በመማር ሂዳት መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን ድንቅነህ (2011) በመግለፅ አንድን ነገር የማከናወን ፍላጎትና በረስ መተማመን የሚጨምር ልዕለ አዕምሮአዊ የመነቃቃት ተግባር መሆኑን ገልጿል፡፡ በዚህም የማንበብ ተነሣሽነት ከማንበብ ጋር ጥብቅ የሆነ ዝምድና እንደላቸውም አሣይቷል፡፡ የምሁራንን ሀሣብ መነሻ በማድረግም ተነሣሽነታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች ተነሣሽነታቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ተማሪዎች የበለጠ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ አስቀምጧል፡፡

የመማር ተነሣሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታን በተመለከተ የተለያዩ አጥኚዎች በተለያየ መንገድ ምርምሮችን አካሂደው የተለያዩ ውጤቶች ላይ ደርሠዋል፡፡ በዚህም በውስጣዊ እና በውጫዊ ተነሣሽነት ያላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር

ያለው ተዛምዶ ልዩነት እንዳለው አሣይተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ዘሪቱ (2004) በተነሣሽነት አይነቶችና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል ዝምድና መኖሩን አሣይታለች፡፡ መሪነሽ(2004) የማንበብ ተነሣሽነት ከፍ ሲል የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሚጨምር በመግለፅ የማንበብ ተነሣሽነት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ሚና እንዳለው ገልፃለች፡፡ እቴነሽ (2010) የማንበብ ልምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከፍ ለማድረግ ትልቅ ሚና እንዳለው አሣይታለች፡፡

ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች በከፊል ይህን ጥናት የሚመስሉት ቢሆኑም የመማር ተነሣሽነትን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አለማዛመዳቸው ለዚህ ጥናት መካሔድ ምክንያት ነው፡፡ የውጭ ጥናቶችን በምንመለከትበት ጊዜ Knoll (2000) ተነሣሽነትና አንብቦ መረዳት ተዛምዶ እንዳለቸው በመጥቀስ በተገኘው የጥናት ውጤት ዝቅተኛ ተነሣሽነት ያለቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳላቸው አስቀምጧል፡፡ Hassan and Ramili ማሪዎች የተለያየ ተነሣሽነትና የተለያየ የአንብቦ መረዳት ተሰጥኦ እንዳላቸው አሣይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች የመማር ተነሣሽነት፣ የማንበብ ተነሣሽነት፣ የማንበብ ልምድ፣የማንበብ ብልሃት የሚሉ ሲሆኑ ይህን ጥናት እንደተዛማጅ ቅኝት በመሆን ሲያገለግሉ በአነሡት ጭብጥ እና ባገኙት የጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሣሠሉ ሳይሆን በከፊል የሚገናዘቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህን ክፍተት በመያዝ በተማሪዎች የመማር ተነሣሽነት እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመርመር ይህ ጥናት ተካሂዷ፤ የሚሞላው ክፍተትም ይህ ነው፡፡

በዚህ መሰረት አጥኚዋ በክፍል በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የተማሪዎች የተሳትፎ ማነሥ፣መሰላቸት፣ትምህርቱን የመሸሽ እና ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ በስተማረችባቸው ዘጠኝ አመታት አስተውላለች ፡፡ ለዚህም የተማሪዎች የመማር ተነሣሽነት እንደ አንደ ችግር ሊሆን ይቸላል ብላ በማሰቧ ይህ ተነሣሽነት ማጣትም በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተፅዕኖ ስለ ሚያሳድር የሁለቱን ዝምድና ለመርመር ተነሣስታለች፡፡ በተጨማሪም ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች አብዛኛዎቹ በአፍፈት ተማሪዎች ላይ የተጠኑ በመሆናቸው እና አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ላይ የተጠኑ ጥናቶች አናሣ በመሆናቸው ለዚህ ጥናት መካሔድ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪጥ ያቄዎች

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የጥናቱን ዋና አላማ ከግብ ለማድረስ ይህ ጥናት ከዚህ በታች ለቀረቡት መሪ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ተማሪዎቹ  አማርኛ ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነት አላቸውን?
- የተማሪዎቹ  የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ይመስላል?
- የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታቸውጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል ?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 ዐብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደ ሚመስል መመርመር ነው፡፡ ይህን ከግብ ለማድረስ እና መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚከተሉትን ንኡሳን ዓላማዎች ተዘርዝረዋል፡፡

### 1.4.2 ንኡሳን ዓላማዎች

- ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት ይፈትሻል፤
- የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን እንደሚመስል ይፈትሻል፤
- የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ይመራምራል፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ  ጥናት በዋነኛነት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር እና ለፈለጉት አላማ ግብ መሳካት  እንዲሁም አንብበው መረዳት የሚችሉ ሲማሩ መሆኑን ለመማር ደግሞ ተነሳሽነት አስፈላጊ መሆኑን ተረድተው ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ያግዛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

መምህራን ታላሚውን ቋንቋ ከግብ ለማድረስ እና የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሳካት የተማሪዎች ተነሳሽነት ወይም አዎንታዊ አመለካከት ወሳኝ ሚና እንዳለው በመረዳት የተለያዩ ዘዴዎችን በመፍጠር የተማሪዎቹን ተነሳሽነት ሊያጠናክር በሚችል መልኩ እንዲያስተምሩ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍ ለማድረግ እና ለማሻሻል ወላጆች ለቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጡት ግምት እና ያላቸው አመለካከት ለታላሚው ቋንቋ

በቤት ውስጥ የሚሰጡ አስተያየቶች በተማሪዎች ላይ አወንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖ ስለ ሚያሳድር ወላጆች ይህን አመለካከት በበጎ ጎኑ ቢመለከቱት ተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነታቸው እና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እንደሚጨምር የመፍትሔ ሃሳብ አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸውን ተዛምዶ ለመመርመር ያግዛል፣ በመማር ተነሳሽነት እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ዙሪያ ለሚሰሩ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሃሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቸ ለትምህርት ውጤት ወይም መማር ስላለባቸው ብቻ እንዲሁም ከክፍል ወደ ክፍል ለመሽጋገር ብቻ ሳይሆን በበጎ አመለካከትም ጥልቅ ፋላጎት አሳድረው ትምህርቱን እንዲቀበሉ የመፍትሔ ሀሳብ ይጠቁማል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በኢሉአባ ቦራ ዞን በሁሩሙ ወረዳ ሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዞኑ 14 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በወረዳው ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ያሉ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ካሉ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በ2014 ዓ.ም ለመማር የተመዘገቡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ የሚወሰን ነው፡፡

ጥናቱ ከይዘት አኳያ ሲታይ ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ምን ይመስላል? የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? የመማር ተነሳሽነታቸው ከአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ያለው ተዛምዶ አወንታዊ ነው ወይስ አሉታዊ የሚሉ ነገሮችን ብቻ የሚያይ ሲሆን ተለዋዋጮቹም ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ እነሱም የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ነፃ ተለዋዋጭ ሲሆን የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ደግሞ ጥገኛ ተለዋዋጭ ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት ችሎታቸው የሚወሰነው በተነሳሽነታቸው ስለሆነ ነፃ እና ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት በፅሁፍ መጠየቅ የተሳካ ሲሆን የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ደግሞ ፈተና ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የመማር ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመሆኑ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎች እና የቋንቋ እውቀቶችን አይመለከትም፡፡ በተጨማሪም ከተነሳሽነት አንፃር ውጫዊ እና ውስጣዊ ተነሳሽነት እንጂ ሌሎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ለዚህ ጥናት እንደ ተዛማጅ ሊሆኑ የሚችሉ ጥናቶች አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ያለው ተዘምዶ በሚል ርዕስ በባህደር ዩኒቨርስቲ አራት ያላነሱ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህን ጥናቶች እና ሌሎች ተዛማጅ መጻሕፍትን ለማየት ባለው ወቅታዊ ሁኔታ፣ የጊዜ እና የኢኮኖሚ እጥረት አጥኚዋ በቦታው ሂዳ መረጃ ባለማግኘቷ ዉስንነት ታይቶበታል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ተግባራዊ ብያኔ

- **ተዛምዶ** በተማሪዎች የመማር ተነሣሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መካከል የሚኖረን አወታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት ይመለከታል፡፡
- ***ታላሚ ቋንቋ*** ተማሪዎቹ እንዲያውቁት የተፈለገው  ቋንቋ ወይም ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ ነው፡፡
- **የአንብቦ መረዳት ችሎታ** የምንባቡን ጥቅል መልዕክት መረዳትን፣ ከፅሁፉ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ መረጃዎችን መለየትን፣ የመገንዘብ ችሎታ ድምር ውጤት ነው፡፡
- **የመማር ተነሣሽነት** የተማሪዎቹ ውስጣዊና ውጫዊ ስሜት፣ አመለካከት፣ አተያይ፣ ፍላጎት የሚሉትን የያዘ ነው፡፡
- **ውስጣዊ ተነሣሽነት** የተማሪዎቹ የተፈጥሮ ወይም የራሳቸው አተያይና አመለካከት ነው፡፡
- **ውጫዊ ተነሣሽነት** በተለያዩ አካላት ግፊት፣ በመምህራን፣ በወላጆች እና ሰው ሰራሽ ነገሮች የሚፈጠር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ስር ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸዉ መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦችተዳሰዋል። በዚህም የተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ምንነት፣አይነቶች፣ አላማዎች፣ ደረጃዎች የተነሳሽነት ተላዉጦዎች የተነሳሽነት ጠቀሜታ በቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆን የተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ተዛምዶ በንድፈ ሃሳብ እና በፅንሰ ሃሳብ ተደግፎ የቀረበ ሲሆን የቀደምት ጥናቶች በዚህ ርዕሰ ዙሪያ የተሰሩ ተቃኝቶበታል።

## 2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የተነሳሽነት ምንነት

አለምነሽ (2001) ምሁራንን ጠቅሳ እንደገለፀችው ወደ አንድ ግብ ለመድረስ የሚቀሰቅስ ፣ የሚገፋፋ፣ የሚያነሳሳና የሚመራ ውስጣዊ ስሜት መሆኑን ገልፃች። William and Burden (1997) በንቁአዕምሮአንድን ድርጊት ለመፈጸም የሚከወን ጥረት የሚያበረታታ አዕምሮዊና ስሜታዊቅስቀሳነዉ። Woolttolk(2004)የዉስጥ ፍላጎትን ጸባይበ ትክክለኛ መስመር ምንጭ የምናገኝበት ነዉ። Alis(1994)የቋንቋ መማር የህግ ማህበራዊ እና ስነልቦና ዊልሳናት ዝግጅትና ተሳትፎ ልዩነት መፍጠር መሆኑን ይገልፃል። ይህ ዝግጅትና ተሳትፎ የሚፈጠረው በተነሳሽነት መሆኑን እንረዳለን ማለት ነው።

Giikj (2016) የመማር ተነሳሽነት የተማሪዎችን ስነ-አዕምሮ በሂደት ጉጉት እንዲኖራቸው እና ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ ያግዛል። ይህ መነሳሳት አንድ ግብ ላይ ለመድረስ መሰረት እነደሆነ ይገልጻል። አያይዞም ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ታላቅ ሚናን እንደሚጫወት ያስቀምጣል። Baron (1996) በመጥቀስ ደግሞ ተነሳሽነት ውስጣዊ ስሜታቸውን ያለማንም አስገዳጅነት መሳተፍ እናመሪ መንገድ መያዝ ግልጽ የሆነ የአስተዳደር ባህሪን ይፈጥራል።

ተነሳሽነት፡-ግላዊ ብቃት እችላለው የሚል ዓላማን በመያዝ በሂደት ካሰቡት ግብ ለመድረስ መንገድ ቀያሽ ነው። ይህም የግል አመለካከት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለቆሙለት ዓላማ ዘወትር መትጋት እና ግብን ለማሳካት መጣር ማለት ነው።

Feldam (2004) ለእውነተኛ እና ለትክክለኛ ዓላማ ጠንካራ አቋም እና መስመር መያዝ ማለት ነው። ዘሪቱ (2004) ጋርደርንን በመጥቀስ መነሳሳት ያላቸው ሰዎች ዓላማቸውን ለማሳካት ጥረት ሊያሳዩ ይችላሉ፤ጥረት የሚያሳዩ ተማሪዎች ሁሉ ግን ተነሳሽነት አላቸው ማለት አይደለም። በቋንቋ ትምህርት አስገዳጅ ሁኔታዎች (መምህርን ወይም ወላጅን

የማሰገንዘብ ፍላጎት፣ ወላጅን ማስደሰት ምኞት እና ከፍተኛ ውጤት ማምጣት) ተማሪዎች ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ግለሰብ ቋንቋን ለመልመድ ሊፈልግ ይችላል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም በሚያደርጋቸው ተግባራት ሊደሰት ይችላል፡፡ ፍላጎቱና የደስታ ስሜቱ ጥልቅ በሆነ ፍላጎት ካልተደገፉ ግን ተነሳሽነቱን አያመለክትም ስለዚህም ዓላማን የማሳካት ምኞትና ለዓላማው የሚኖሩት በጎ አመለካከቶች ከጥረት ጋር ሲገናኙ ብቻ ነው፡፡ስለዚህ እንደ ምሁራኑእና እንደ ዘሪቱ አባባል ለዓላማ መቆም እና ፍላጎት መኖር ብቻ ሳይሆን ዓላማን ከበጎ አመለካከት ጋርማዋሀድ መቻል አለብን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ዓላማችን ውጤት ብቻ ከሆነ ተነሳሽነቱ ያለንም አመለካከታችንን ማስተካከል እና በጎ ማድረግ አለብን ማለት ነው፡፡

መሪነሽ (2004) ኖኤልስ እና ቢልን በመጥቀስ ቋንቋ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚገኘው የባህሪይ ለውጥ የተነሳሽነት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት ከኖረው ሠፊ ግንዛቤ ያለው፣ ትውስታ ያለው እና አዕምሮአዊ ዕድገቱ የተፋጠነ ስለሚሆን ካለመው ግብ ይደርሳል፡፡

Zareian&Jodei (2005) ተነሳሽነት የተማሪዎችን ጎደሎ አሰተሳሰብ በማስቀረት ለመልካም ውጤት የሚያበቃ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከሀሳቡ እንደምንረዳው የተማሪዎች ግንዛቤ እና የባህሪይ ለውጥ ተነሳሽነትን የሚያመላክት ነውማለት ነው፡፡ ስለዚህ ተነሳሽነት አዕምሮአዊ ዕድገትንና አስተሳሰብን መሰረት ያደረገ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በአጠቃላይ ተነሳሽነት ሙሁራንና ተመራማሪዎች በተለያየ አገላለጽ ይግለጹት እንጅ አብዛኛዎቹ ሙሁራን እንደ ተስማሙበት ተነሳሽነት ማለት ፍላጎት፣ ፀባይ፣ ምኞት፣ አስተሳሰብ፣ አተያይ እና አመለካከት ማለት ሲሆን የተማሪዎች ሁኔታ እና ፀባይ እያስተማርን በመማር ማስተማር ሂደት በዉስጣቸዉ ያለውን ስሜት የምንለይበት ሂደት ነው፡፡

## 2.1.2 በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተነሳሽነት ጠቀሜታዎች ወይም ሚና

የተነሳሽነትን ጠቀሜታ Dornye (2009) ተነሳሽነት የ2ኛ ቋንቋን ለማስተማር እና የተሻለ የመማር ማስተማር ሂደት ለመፍጠር ታላቅ ሚናን ይጫወታል፡፡ ተነሳሽነት የ2ኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለዉን ጠቀሜታ በ3 መንገድ አሰቀምጧል፡፡

1. ተማሪዎች የ2ኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸዉን ሙሉ ስሜት እንዲሁም ብቁ ችሎታ በመለየት እና ቋንቋዉን መናገራቸዉ መነሻ አድርገን ትክክለኛና ተስማሚ የሆነ ምላሽ የምናገኝበት ነዉ፡፡
2. ተማሪዎች የራሳቸዉ ዉስጣዊና ዉጫዊ ግፊት ተጠቅመዉ የይቻላል መንፈስን ይዘዉ ለዉጤት የሚደረሱ መሆኑን Do'mye (2005) በመጥቀስ ገልጿል፡፡

3. ተማሪዎች ከልምድና ከአካባቢዉ ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመዉ ልምድ የሚያገኑበት ነዉ፡፡

McClellendand (1976) ተነሳሽነት የመማር ማስተማርን ሂደት ለማሳካት አዕምሮን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለዉ ገልጿል፡፡ Haward and Bray(1989) የስራን ሁኔታ ለመከታተል እና ዉጤት ለማምጣት ጠቃሚ መሆኑን ይገልጻል፡፡ Ellis(2008) ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሲማሩ የተማሪዎቹን ችሎታ ድርሻ ግላዊ ብቃት፣ ስነ አዕምሮአዊ ምክንያትና ግላዊ ልዩነት ለማወቅ ያስችላል፡፡ ድንቅነህ (2011) ተነሣሽነት በመማር ሂደት ብቻ ሳይሆን በማንብ ሂደትም መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ምክንያቱ አንድን ፅሁፍ ለማበብም ሆነአንብቦ ለመረዳት እውቀት ወይም ግንዛቤ ብቻ ሳይሆን ተነሳሽነትም ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በሌላ መልኩ ተነሣሽነት አንድን ነገር የማከናወን ፍላጎትና በራስ መተማመን የሚጨምር ልዕለ አዕምሮአዊ የመነቃቃት ተግባር መሆኑን ገልጿል፡፡

በቀለ (2009) የተነሳሽነት ሚና የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሶ የተነሳሽነት ሚና በአማርኛ ትምህርት ውስጥ በሚል እንደሚከተለው ገልጿል፡፡ የቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደትን ከዳር ለማድረስ የቋንቋ መምህሩ የተማሪዎችን ና የሌሎች አጋዥ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ Stren (91983) እና Ur (1996) እንደገለፁት በጥንት ጊዜ የቋንቋ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በመምህሩ አማካኝነት ብቻ ነበር፡፡ይህ አይነት መምህር ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በአሁኑ ጊዜ በተማሪው ተሳትፎ ተተክቶ ይታያል፡፡ ተማሪው በቀጥታ ከመምህሩ ከሚማር ይልቅ በክፍል ውስጥ ለሚደረገው ተግባራዊ ተሳትፎ ትኩረት መስጠት የአስተምህሮቱ ሂደት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ተማሪው የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ሂደት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋ ተግባቦት ሂደትም ላይ መሆኑን ይገልጹልናል ፡፡

Narden and Lin (2000) የተነቃቁና ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በቋንቋ ክንውን ላይ ሙሉበሙሉ ተሳትፎ ስለሚያደርጉ ተነሳሽነት ከሌላቸው ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ክሂሎታቸውን ለማሳደግ የተሻለ ዕድል እና አጋጣሚ አላቸው፡፡

Gardener&Lambert(1972) በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ቋንቋ መልመድ ወይም መማር ማለት ካለው ጠቀሜታ አንፃር ሲታይ "ማህበረሰቦችን እንደሚያገናኝ ድልድይ ይቆጠራል፣" በተግባቦቱም ረገድ ግለሰቡ ያለው ተነሳሽነት ለቋንቋው ማደግም ሆነ ውድቀት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

### 2.1.3 የተነሳሽነት ዓይነቶች

በየጊዜው የሚነሱ ምሁራንና አጥኚዎች የተነሳሽነትዓይነቶችን በተለያየ መንገድ ብዙዎቹ የተስማሙበት እና ብዙዎችን ተነሳሽነቶችን ሊያጠቃልሉ የሚችሉ ሁለት የተነሳሽነት ዓይነቶችን በማስቀመጥ ሁሉም ይመሳሰላሉ፡፡ እነሱም Intrinsic motivation & Extrinsic motivation (ውስጣዊ እና ውጫዊ) ተነሳሽነት በማለት ተከፍለዋል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት ተፈጥሮአዊ እውነተኛ ሲሆን ውጫዊ ግን ሰው ሰራሽ ስለሆነ በቤተሰብ፣ በሌሎች ሰዎች፣ በመምህራን እና በተለያዩ አካላት ግፊት ወይም ቀስቃሽነት ሊፈጠር የሚችል ነው፡፡

Ellis(1995),(1994),Garder(1985) ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የሚማሩበት የራሳቸዉ የሆነ አላማ ይኖራቸዋል፡፡ ከአላማዎቹ ዋና ዋናዎቹ ከታላሚዎቹ ቋንቋዎችና ከተናጋሪዎቹ ጋር ማህበራዊ ዉህደት ለመፍጠር ካልሆነም በቋንቋዉ ጥቅማጥቅም ለማግኘት ይህም ስራ ለመቀጠር፣ ንግድ ለመነገድ ወዘተ ሊማሩ ይችላሉ በማለት ያስረዱናል፡፡ Noels(2001) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ገፅታ በመደነቅ፣ ወዳጅነት ለመፍጠር፣ አዕምሮአዊ ችሎታን ለመፈተሽ ወዘተ አላማዎች ሲሉ ታላሚዉን ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ ሊማሩ እንደሚፈልጉ ይገልፃሉ፡፡

#### 2.1.3.1 ዉስጣዊ ተነሳሽነት

ዘሪቱ (2004) ሰዎች የሚከናውኑት ተግባር ስለአንድ ነገር ለማወቅ ለመረዳትና ደስታ ለማግኘት ከሆነ ተግባራቸው ውስጣዊ ተነሳሽነትን መሠረት ያደረገ መሆኑን ገልጻለች፡፡

አማረ (2011) ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያለዉ የቋንቋ ተማሪ ታላሚዉን ቋንቋ የሚማረዉ በተማሪዉ ቋንቋ አንዳች ጥቅምን ፈልጎ ወይም ሌላ በስተጀርባዉ የሚገፋፋዉ ሀይል ኖሮት ሳይሆን ቋንቋዉን በመማሩ ከሚሰማዉ ዉስጣዊ እርካታ በመነሳት በግሉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን ለማሳካት ትኩረት የሚያደርግበት ነዉ በማለት ገልጿል፡፡

Zareian&Jodei (2015) ውስጣዊ ተነሳሽነት ማለት ከአንድ ግብ ላይ ለመድረስ በራሳችን ያለማንም አስገዳጅነት የምናከናውነው ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ካሰብንበት ግብ እና ውጤት ለመድረስ ቆራጥ መሆን እንዳለብን ያስረዳሉ፡፡ ይህን ለማድረግም ሚከተሉትን የተነሳሽነት ናሙናዎች አስቀምጧል፡፡

- ሁልጊዜ በት/ቤት በመገኘት የሴሚስቴሩን ትምህርት መማር መቻል
- ብዙ ጊዜ በትምህርት ደራሲ መሆን ምሁራንን በመንገር ማነሳሳት ለምሳሌ፡- አስትሮኖሚ፣ ስነ-ፈለክ ተመራማሪዎችን ማሳወቅ

GiiRj (2016) ውስጣዊ ተነሳሽነት በግል እውነተኛ እና ጠንካራ አላማ በመያዝ የራስን ስራ መፈጸም እንደሆነ በመግለጽ ያለማንም አስገዳጅነት በራስ ሀሳብ እና ፍላጎት ለቆምንለት ዓላማ ተሳታፊ መሆን እንደሆነ ይገልጻል፡፡

GliRjLongnathan (2016) ዉስጣዊ ተነሳሽነት የተማሪዉ ዉስጣዊ ስሜት፣ሃሳብ፣ ተሳትፎ፣ እና የስራ ፍቃደኝነት ነዉ፡፡ Ahmad (2013) ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያለምንም አስገዳጅነት በራስ ምኞት ፍላጎት ትምህርቱን መርጦ አዕምሮዉ በፈቀደለት መንገድ የሚማረዉ ነዉ፡፡ RyanandDec (2000) ሽልማቶች በማየት ሳይሆን እንደየሁኔታዉ ዉስጣዊ የሆኑ የሚማርኩ እና የሚስቡ አመለካከቶችን ማንጸባረቅ መቻል ነዉ፡፡

Ahmad, anda Pourhossen (2012) ዉስጣዊ ተነሳሽነት ምክንያታዊ የሆነ ሃይል ፍላጎትና ተሳትፎ በመሆኑ ግላዊ ብቃትን የሚያካትት ነዉ፡፡ ዉስጣዊ ፍላጎት እና ፀባይ በትክክለኛ መስመር ምንጭ የምናገኝበት ነዉ፡፡ Ahmed (2013) በሚሰራዉ ስራአጋዥ ምክንያት፣ ሽልማት፣ ዉጫዊ ግፊት ማበረታቻ እና እርዳታ የሚያስፈልገዉ መሆኑን ገልጿል፡፡

እንደ ምሁራኑና አጥኚዎቹ ሀሳብ ውስጣዊ ተነሳሽነት በተፈጥሮ የምናገኘው እና በራሳችን ግፊት፣ ፍላጎት እንዲሁም ዓላማና ግብ ለማሳካት የምናደርገው ጥረት ነው፡፡ ስለዚህ ውስጣዊ ተነሳሽነት ካለ ለጥሩ ውጤት መነሻነት መሠረት ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ለመማርም ይኸው ተነሳሽነት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በተፈጥሮ የተሰጠንን ተነሳሽነት በበጎ አመለካከት በማገዝ በታላሚው ቋንቋ ትኩረት የምንሰጥበት እና ለጥሩ ውጤት የምንበቃበት መሆን አለበት፡፡

በቀለ (2009) Noels (2003)ን በመጥቀስ የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ከራሳቸው የሚመነጭ በመሆኑ መምህሩ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን እንዲማሩና እንዲከታተሉ በማንኛውም መንገድ እንዲገፋቸው እና እንዲጎተጉቷቸው አይጠበቅበትም፡፡ ተማሪዎች ፍላጎታቸውን ለመፈፀም በማንኛውም ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያገኙት ከአንድ አቅጣጫ ወይም ከራሳቸው ስለሚሆን የመድረሻ ግብ የተወሰነ ሊሆን ይችላል፡፡

Harmer (1991) ቋንቋ በመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች የሚደረግ ውጫዊ ተነሳሽነት እምብዛም ባለመታየቱ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት አሉታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ይታያል፤ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም ለቋንቋ ትምህርት ስኬታማነት ስለሚያግዝ በቋንቋ ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ በሚችሉ ተለዋዋጮ ማለትም በመምህሩ በማስተማር ዘዴው እና ተማሪዎች በሚያገኙት ውጤት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

Noels (2000)ን በመጥቀስ ደግሞ ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ሰዎች አንድን ተግባር ለመምረጥም ሆነ ለማከናወን ነፃነት አላቸው፡፡ በተጨማሪም የችሎታ ብቃታቸውን ስለሚያጎለብቱ ፈታኝ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳት እና ችግሮችን ማቅለል ይችላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ የውስጣዊ ተነሳሽነት አቅጣጫዎችን በሚከተለው መንገድ አስቀምጠዋል፡፡

1. እውቀትለማግኘት፡-ግለሰቡ ከአዳዲስ ሀሳቦች ጋር እራሱን ለማስማማትና ተግባሮችን ለማከናወን እንዲሁም እውቀትን ለማሳደግ ሲል ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖረዋል፡፡
2. ተግባርንለመፈፀም፡- ግለሰቡ አንድን ነገር ለማማከር ወይም ለማከናወን እንዲሁም ውጤታማ የሆነ ግብ ላይ ለማድረስ ተነሳሽነት ይኖረዋል፡፡
3. ለማነቃቃት፡-ግለሰቡ አንድን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት ደስታን፣አድናቆትን፣ እርካታን ወዘተ ለማግኘት ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖረዋል፡፡ በማለት አስቀምጧል፡፡ይህም የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር እና ለተማሪዎች አላማ ግብ መምታት እንዲሁም ለውጤታማነታቸው ከፍተኛ ሚና እንዳለው እንረዳለን ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተማሪዎች የውስጣዊ ተነሳሽነት ጉልህ ሚናን ይጫወታል ማለት ነው፡፡

## 2.1.3.2 ውጫዊ ተነሳሽነት

ውጫዊ ተነሳሽነት ውጫዊ ባህሪ ወይም ሰው ሰራሽ ግፊትን መሠረት ያደረገ ነው::

Zareian&Jodei (2015) ውጫዊ ተነሳሽነት የራስን ዓላማና በተጨማሪም ውጫዊ ምንጮችን ወይም መነሻ ሀሳብን የሚፈልግ ነው፡፡ ይህም ጥሩ ነጥብ ወይም ውጤት ካመጣ ልዩ ስጦታ እንደሚዘጋጅ እና እንደሚያገኝ በማነሳሳት ከቤተሰብ ወይም ከሌሎች አካላት የሚደረግ ነው፡፡ GiiRj (2016) ውጫዊ ተነሳሽነት በተመለከተ አከባቢያዊ ሀይልን አይተው ገንዘብ፣ ምግብ፣ ዕውቅና ወዘተ አከባቢያዊ መመሪያን ተከትለው ግባቸውን የሚያሳኩበት ነው፡፡ ለስራቸው ውጤትም ከውጫዊ አካል ሽልማት ይፈልጋሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ወላጆች፣ መምህራን፣ በቀጣሪዎችእና ከመሳሰሉት ሽልማትን በመጠበቅ ይነሳሳሉ፡፡ ከተለያዩ አካላት ሽልማት፣ማበረታቻ፣ጭማሬ፣ በደመወዝ፣ በምስጋና፣ በአድናቆት እና በደረጃ ዕድገት የሚበረታታ ተነሳሽነት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

ዘሪቱ (2004) ውጫዊ ተነሳሽነት በሚፈጠርበት መንገድ በሚየሳካው ግብ ከውስጣዊ ተነሳሽነት የሚለየው በመምራን፣ በወላጆች፣ በጓደኞች ወይም በሌላ አካል ለመወደስ ሽልማት ለማግኘት ፣ ለመመስገን በፈተና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ወዘተ ባሉውጫዊ ጉዳዮች እንደ ሚጠናከር አስቀምጣለች፡፡ በአጠቃላይ ውጫዊ ተነሳሽነት ከውጭ ሀይሎች ማበረታቻ እና ሽልማት የሚያበረታታ እና ከግብ ለመድረስ ውጫዊ ግፊትን የሚፈልግ

መሆኑን እንገነዘባለን። ከነዚህ ተነሳሽነቶች በተጨሪም አንዳንድ ምሁራን ውህዳዊና ጥቅማዊ ተነሳሽነተቶች ብለው የሚጨምሩ አሉ። ሀሳባቸውንም እደሚከተለው ይገልጻሉ።

Ahmed(2013) ተማሪዎች በሚኖሩበት እና በሚገኙበት አካባቢ ያለዉ ማህበረሰብ የሚነገረዉ ቋንቋ እና ባህል መስለዉ በመኖር ዉህደት ይፈጥሩ እና ቋንቋዉን ይለምዱታል፤ይናገሩታል። አማረ(2011) ጥምረታዊ በማለት ጠንካራ ተነሳሽነት እንደሆነ ገልጿል።ይህም ተማሪዎች ሆነ ብለዉ ተግብቦት ለመፍጠር የሚለምዱት ስለሆነ ነዉ። ዉህዳዊ ተነሳሽነት ያለቸዉ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘላቂነት ያለዉ የመማር ስኬት እንዳላቸዉ ይናገራል። አንድን አላማ ለማሳካት፣ ስራለማግኘት፣ ለምረቃ፣ የቀለም ትምህርት ለማወቅ፣ የሚደረግ ተነሳሽነት ነዉ። ከሙሁራኑ እና ከተመራማሪዎቹ ሃሳብ እንደምንረዳዉ የተነሳሽነት አይነቶች በተለየ አገላለፅ ይግለጹዋቸዉ እንጂ በዉስጣዊ እና በዉጫዊ ተነሳሽነት በተለያየ መንገድ ይጠቃለላሉ። የሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ግን ከሁሉም ቋንቋ የበለጠ ውስጣዊ ተነሳሽነት ቢኖራቸዉ የመማር ማስተማሩ ሂደት የበለጠ ዉጤታማ እንደሚሆን አብዛኛዎቹ ይስማማሉ።

Vanlier (1988) "ውጫዊ ተነሳሽነት በስራ ላይ ለመዋል እንደ ተበደሩት በኃላም እንደሚከፍሉት ገንዘብ ይቆጠራል" ይህም ማለት ከውስጣችን ሳይሆን በሌላ ሰው ወይም በውጫዊ ነገሮች ግፊት የሚመነጭ መሆኑን ያመለክተናል። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸው ትምህርት ስቢቸው ወይም አንጉቶአቸው ሳይሆን በተለያዩ ሁኔታዎች እና አካላዊ ግፊት እንደሆነ እንረዳለን። ይህም ከመምህራን፣ ከወላጆች፣ ከጓደኞች፣ የሚገኙ ሽልማቶች፣ ምስጋናዎች፣ ምጋቤ ምላሾች ማነቃቂያነት የሚፈጠር መሆኑን Brown (1987) Ur (1996) ያስረዳሉ።

Ellott etal (2005) Noels (2009) በውጫዊ ተነሳሽነት የሚገኝ ግብ የተለየ ነው። ተማሪዎች ውጫዊ ተነሳሽነትን ያካበቱት ከሆነ በፈተና ጥሩ ውጤት ማግኘት፣ ጥፋትን በመቀነስ፣ ቅጣት ማስቀረት እና የመሳሰሉትን የአጭር ጊዜ ግቦች ያገኛሉ በማለት ገልጸዋል።

Doumyei (1998) ተነሳሽነት ሶስት ደረጃዎች እንዳሏቸው አስቀምጧል።

1. በውጫዊ ተፅዕኖ የሚፈጠር ተነሳሽነት ከግለሰብ ውጭ በሆኑ ምንጮች ላይ የተመሰረቱ ተግባራት ናቸው። ይህም ጥቅማጥቅምን መሠረት ያደረገ ነው።
2. ከራስ በሚመነጭ ጫና የሚፈጠር ተነሳሽነት ተማሪዎች አንድን ተግባር ሊያከናውኑ ሲሉ ከራሳቸው ጋር የማይጣጣሙ ግለሰቦች ግርታዎች እንዲኖራቸው ያደርጋል። ምንም እንኳን የግፊቱ ምንጮች አስፈላጊ ቢሆኑም ተማሪዎቹ የራሱን እድል በራሱ

የመወሰን እድላቸው አናሳ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይህም ሲባል ጓደኛ አይተው እንደ ሰው ልሁን በሚል ሊፈጥሩት የሚችሉት ማለት ነው፡፡

## 2.1.4 የተነሳሽነት መገለጫዎች

አማረ (2011) የተለያዩ ሙሁራንን ሐሳብ መነሻ በማድረግ የተነሳሽነት መገለጫዎችን በሶስት ክፍሎች መድቧቸዋል፡፡

### ሀ. ግለ ብቃት (self eficancy)

Bandura (1986) ግለብቃት አንድን ተግባር በሚፈለገው መልኩ ከመፈጸም አኳያ የሚሰጥ ግላዊ ውሳኔ ነው፡፡ Ehrman (1996) ተማሪዎች በመማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ያላቸው የመቋቋም ችሎታን የሚመለከት ነው፡፡

### ለ. ግለ መር (self-Relation)

Zmmerman (2008) ተማሪዎች በተለያዩ የዕለታዊ ገጠመኞች ወይም ክንውኖች ያገኟቸውን አቅሞች (ቃላዊ አመለካከቶች) ወደስነ ትምህርታዊ ችሎታ ለመለወጥ ጥረት የሚያደርጉበት ነው፡፡ shunk and Zimmerman (1994) ራስን መምራት ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ ተማሪዎች እራሳቸውን የሚቆጣጠሩበት እና የሚገምግሙበት ሂደት ነው፡፡

### ሐ. ግለ ግንዛቤ (self-concept)

Pajars and schank (2001) ግለግንዛቤ በጥቅል አስተሳሰባዊ እምነቶች ላይ ትኩረት ሲያደርግ ግለብቃት ግን ሊለኩ የሚችሉ ዝርዝር አላማዎችን ከማከናውን አንፃር የሚታይ መሆኑን ምሁራኑን መሰረት አድርጎ ገልጿል፡፡

## 2.1.5 የተነሳሽነት ተላውጦዎች

ቋንቋን በማስተማር ሂደት የቋንቋ ተነሳሽነትን ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ተላዉጦዎች እንዳሉ በቀለ (2009) ምሁራንን በመጥቀስ አስቀምጧል፡፡

1. ማህበረሰቡ ለቋንቋ ያለዉ አመለካከት፡-በትምህርት ቤት ዉስጥ የሚሰጠዉ ቋንቋ የራሱ የሆነ አመለካከት ይኖረዋል ይህም ሲባል ከክፍለ ጊዜ መደልደል ጀምሮ ትኩረት ያለመስጠት የሚለዉን ያካትታል፡፡

ተማሪዎቹም ቋንቋን ለመማር ምን ያህል ፍላጎት አላቸዉ? የሚሉ ጥያቄዎች የማህበረሰብን አመለካከት ምን አይነት እንደሆነ ሊያንፀባርቁ ይችላሉ፡፡

ተማሪዎቹ በማህበረሰቡ ለቋንቋው የሚሰጠዉን አመለካከት በመያዝ በቋንቋት ምህርት ላይ ያላቸዉ ተነሳሽነት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከማህበረሰቡ ጋር ለረጅም

ጊዜ አብረዉ የኖሩ በመሆናቸዉ የማህበረሰቡ አመለካከት ሊንፀባረቅይችላል:: በማለት Harmer(2001)ን ጠቅሶ ገልጿል:: ይህ ማለትም የማህበረሰቡ አመለካከት በተማሪዎች ላይም ሆነ በታላሚዉ ቋንቋ አሉታዊ እና አወንታዊ ተጽኖ ሊያሳድር ይችላል ማለትነዉ::

2. ወላጆች በቋንቋ ትምህርት የሚሰጡት ግምትና ያላቸዉ አመለካከት፡-ወላጆች ለታላሚዉ ቋንቋ በቤት ዉስጥ የሚሰጡት አስተያየት በተማሪዎች ላይ አወንታዊና አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸዉ የማድረግ ሚና አለዉ:: ይህ ማለት ወላጆች ልጆቻቸዉን ሲከታተሉ ለታላሚዉ ቋንቋ አሉታዊ አመለካከት እና ዝቅተኛ ቦታ ካላቸዉ ተማሪዎችም የሚኖራቸዉ አተያይና አመለካከት የወረደ ይሆናል ማለትነው::

3. ቢጤዎች ለቋንቋ ትምህርት የሚሰጡት ግምት፡- በአንድ ክፍል ዉስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች የተለያዬ አመለካከትና ግምት አላቸዉ:: ስለሆኑም በክፍል ዉስጥ ለሚያከናዉኑት ተግባራት አወንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች አላቸዉ:: ይህ ማለት ደግሞ የተለያዩ አመለካከት ያላቸዉ ተማሪዎች ለዚያ ቋንቋ የተለያዩ አሉታዊ ጎን የሚያወሩ ከሆነ አመለካከታቸዉና አተያያቸዉ ከወረደ ቋንቋን የመማር ፍላጎት አይኖራቸዉም፤ ይህ ማለት ደግሞ ተነሳሽነት የላቸዉም ማለት ነዉ::

4. የቋንቋ መምህሩ፡- አማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን የሚያስተምረዉ መምህር በተለያየ መልኩ የተማሪዎቹን ተነሳሽነት ሊያጠናክር በሚችል መልኩ መሆን አለበት:: ይህም ሲባል በመጀመሪያ መምህሩ ለራሱ ለታላሚዉ ቋንቋ በጎ አመለካከት ሊኖረው ይገባል:: ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ማስተማር ሳይፈልግ ለደመወዝ ወይም ከእኔ ላይ ይዉረድ በግብር ይዉጣ የሚያስተምር ከሆነ አስቸጋሪ ነው፡፡ UR(1996) Pintrich &Schunk(2002) የመምህሩ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ሲገልጹ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማጎልበት መምህሩ ትልቅ ሚና እንዳለዉ ያስረዳሉ:: ስለሆነም መምህራን ተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመፍጠር ማስተማር እንዳለባቸዉ እንረዳለን ማለት ነዉ::

5. የማስተማሪያ ዘዴ፦ የቋንቋ መምህሩ የቋንቋ ትምህርቱን የመማርማስተማር ሂደቱን ስኬታማ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡ ይህም ሲባል የትምህርት አቀራረቡ የተማሪዎቹን አካባቢያዊ ዳራ፣ የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ ፍላጎታቸውንና አመለካከታቸዉን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት ማለት ነው::

6. የቋንቋ ትምህርት ትግበራዎች፦ ለማስተማሪያነት የሚቀርቡት ክንዉኖችና መልመጃዎች ርዝማኔና ዉስብስብነት የሌላቸዉ መሆን አለባቸዉ:: ይህም ሲባል የሚቀርቡት ተከታታይ ምዘናዎች የእነሱን ሁኔታዎች ያገናዘበ መሆን አለበት:: ይህንንም Ur (1996) Prntrich

and Schunk (2002) በትግበራዎች በአማካይነት የተማሪዎች ተነሳሽነት ሊቀንስ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

## 2.1.6 የአንብቦ መረዳት ምንነት

አደይ(2012) የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት(1999)ን በመጥቀስ እንደገለፀች 'ንባብ በፅሁፍ ላይ የሠፈረን ነገር በአንደበት ወይም በድምፅ አማካኝነት ጮክ አድርጎ ማንበብ፣የመናገር እና የመስማት ድሪጊት በቤተ-ክህነት ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚስጥ የአነባበብን ጥሬትና ፍጥነትን የሚመለከት ትምህርት ነው' በማለት መፈታቱን ገላፃለች፡፡ አሰጋ ለማ እና ታደስ ሲባም(2011)ን በመገልፅ አነባበብ የሚለው ቃል ደግሞ "በፅሁፍ ላይ የሠፈረን ነገር ድምፅ እያሰማ በአንደባቱ አለ ተናገረው ወይም ድምፅ ሣያሰማ በአዕምሮው ዘለቀው ማለት እንደ ሆነ ገልፃለች፡፡

ስለዚህ ንባብ ቃላትን ከመረዳት የሚጀምር ሂደት መሆኑን በመግለፅ በንባብ ክሂል ዙሪያ የጥናት ትኩረታቸውን ያሣረፉ ምሁራን ስለንባብ ምንነት የተለያዩ ፍቺዎችን አቅርበዋል፡፡ በዚህ መሠረት ንባብን መረዳት መተርጎም፣ መፍታት፣ በስሜት መድረስ፣ መቀበል፣ መገዘብ፣ መለየት፣መገጠል፣መቁጠር እና ድምፅ ማውጣት፣ መናገር ንባብ ከሚሉ ሀሣቦች ጋር በማያያዝ ያቀርባሉ፡፡

መረዳት ግን ከንባብ ባለፈ መሆኑን ለማሰረዳት ንባብ አንድን ነገር ለማወቅ የሚረዳ ክሂል እንደሆነ ተገጿል፡፡ መረዳት የንባብ የመጀመሪያው ደረጃ አለመሆኑን ማወቅም አስፈላጊ ነው፡፡ ንባብ ከመረዳት የተለየ ነው፡፡ መረዳትም ከንባብ የተለየ ነገር ነው ምክንያቱም ንባብ ድምፅ አስመቶ መጥራት ወይም ሁሉንም ሀሣብ መቃኘት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ያነበብነውን ነገር በሙሉ እንረደዋለን ማለት አይደለም፡፡ ይህም ሲባል አንብቦ መረዳት ከማንበብ ባለፈ መተርጎም፣ መገንዘብ፣መቀበልና መልዕክቱን መረዳት መሆኑን አብዛኞች አጥኚች እና ተመራማሪዎች ይስማማሉ፡፡

Pikulsk እናChard,(200)፡፡ አንብቦ መረዳት በማንበብ ትምህርት ውስጥ ወሳኙ ሲሆን ማንኛውም አንባቢ በንባብ ተግባር ውስጥ የሚገባው ለመረዳት ነው፡፡ ስለሆነም ትርጉም ያለው ግንዛቤ እና መልዕክት ለማግኘት አንባቢው ከሚያነበው ፅሁፍ ጋር የሀሣብ ልውውጥ የማስላሰል መስተጋብራዊ ግንኙነት ነው በማለት አደይ (2012) ገልፃለች፡፡በመሆኑም ተማሪዎች የጠለቀእውቀት እንዲኖራቸውና በዚህም በትምህርታቸው የተሻለ ውጤትእንዲያስመዘግቡ ከሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ክሂሎቶች አንዱ የአንብቦ መረዳት ክሂል መሆኑን ገልፃለች፡፡

በአጠቃላይ ማንበብ ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ የዘረፉ ምሁራንና ተመራማሪዎች ያሰረዳሉ፡፡ በመሆኑም አንባቢ ሠዎች ይረዳሉ፣የተረዱ ሠዎች ይገነዘባሉ፤ የተገነዘቡ ሰዎች ብዙ እውቀቶችን ይጨብጣሉ፤ ይመራመራሉ፤ ከአስቡት ግብ ይደርሣሉ፡፡ ስለዚህ ማንበብ ሙሉ ሠው ያደርጋል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለፈተና ውጤታቸው፣ ከክፍል ወደ ከፍል ለመሸጋገር የነገውን ራዕያቸውን ለማሣካት እና ተወዳዳሪ ለመሆን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለማንበብ ደግሞ መነሣሣት አለባቸው ማለት ነው፡፡

Weren(2001) ንባብ የሁለት መሰረታዊ እዉቀቶች ዉጤት ነዉ፡፡ ድምፅ በወካይ ንባብ የሁለት መሰረታዊ እዉቀቶች ዉጤት ነዉ፡፡ ድምፅ በወካይ ምልክቶች አማካይነት የቀረበዉን ጽሁፍ ወደሚወክሉት ንግግር መተረጎም እና ጽሁፉ የቀረበበትን ቋንቋ በበቂ ሁኔታ የማወቅ ችሎታ መሆኑን ከሁለቱ አንዱ ከጎደለ ግን አንብቦ መረዳት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ድንቅነህ (2011) ምሁራኑን መሰረት አድርጎ ጠቅሷል፡፡ አማረ (2011) የሰራው ከመፃፍ ችሎታ ጋር በማዛመድ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የምሁራንና የተመራማሪውን ሐሳብ እንደመነሻ ለመጠቀም ነው፡፡

ፍቅሬ (2012) እንድ ሰዉ ምንባብን የሚያነበዉ በፅሁፉ ዉስጥ ለማግኘት የፈለገዉን መረጃ ለማወቅ ወይም የሚፈልገዉን ጉዳይ መረጃ ለማግነት መሆኑን ጠቅሶ ጋዜጣ የሚያነቡ ሰዎች ብዙ ሲሆኑ ትኩረት ሰጥተዉ የሚያነቡት መረጃ ለማግኘት መሆኑን ገልጿል፡፡

ከሙሁራኑና ከተመራማሪዎች ሐሳብ እንደሚንረዳው ግለግንዛበያቸውን መሠረት በማድረግ ግለብቃትና ግለመር ችሎታቸውን የሚያንፀባርቁበት ነው፡፡ ይህም ሲባል ለመማር ግላዊ ብቃትና ግንዛቤ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ይህን ብቃትና ግንዛበያቸውን ወደተግባር በማምጣት የተገነዘቡትን ወይም አንብበው የተረዱትን የሚገልፁበት፣ የሚተረጉሙበትና ወደውጤት የሚደረሱበት መሆኑን እንገነዘባለን ማለት ነው፡፡

## 2.1.7 የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች እና ደረጃዎች

### 2.1.7.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች

ፍትፍቴ (2010) የምሁራን ሀሣብ በመጥቀስ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶችና ደረጃዎችን እንደሚከተለው አሰቀምጣለች፡፡

Anantasaand kemuning (2016)" Gender Differences in Reading comprenenesion Aclievement" በሚል ጥናት ላይ PEL ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን በሚከተለው መንገድ እንደገለፁአስቀምጣለች፡፡

ክሂል 1፡የምንባብን ፍሬ ሀሣብ መፈለግ (Finding Main idea of the passage) ከቀረበው አጠቃላይ ፅሁፍ ውስጥ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ፈልጎ ማግኘት የቻለ አንባቢ አንብቦ መረዳት ችሏል ማለት ነው፡፡

ክሂል 2፡ በዝርዝር የተቀመጡ መረጃዎችን መፈለግ (finding stated in formation) በዝርዝር የተቀመጡት ሀሳቦች ከጽሁፍ ውስጥ ፍልጎ ማውጣት ከተቻለ ለማንበብ ቀላል ይሆናል ምንባቡንም መረዳት ይቻላል ማለት ነው፡፡

ክሂል 3፡ በዝርዝር ያልጸገለጹ መረጃዎችን መፈለግ (finding unstated information) በዝርዝር ያልተቀመጡ ወይም ያልተዳሰሱ ነገሮች ለይቶ ማውጣት የቻለ አንባቢ የምንባቡን አጠቃላይ አውድ ወይም መተላለፍ የፈለገው ሀሳብ ገብቶታል ማለት ነው፡፡ ስለሆም አንብቦ መረዳት ይቻላል፡፡

ክሂል 4፡ ሊተላለፍ የፈለገውን ሀሣብ መረዳት (finding implied information) አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ በመረዳት ሊተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ መረዳት ከተቻለ እና በራስ አባባል መግለፅ ከተቻለ አንብቦ መረዳት ግቡን መቷል ማለት ነው፡፡

ክሂል 5፡ ከቀዳሚው ሀሳብ ተከታዩን መተንበይ (Preaicing and following pargraph) ከቀዳሚው ሀሳብ ተነስቶ ቀጣዩ ምን ሊሆን እንደሚችል መተንበይ በቀረበው ምንባብ አውድ ወይም ድባብ ሀሳብ ተነስቶ ቀጣይ ምን ሊሆን እንደሚችል የራሳችንን እይታ የምናስቀምንበተ ነው፡፡

ክሂል 6፡ አውዳዊ ፍቺ መፈለግ (finding definition from structural clues) ከቀረበው ጽሑፍ ወይም ምንባብ ተነስተን አገባቡን መሰረት አድርገን ምንባቡ የቀረበበትን አውድ ተርጉመን፣ ምንባቡን ተገንዝበን የምናጎለብትበት ማለት ነው፡፡

ክሂል 7፡ለቃል ክፍሎች ትርጉም መሰጠት (derteminig meaning from wards parts) ምንባቡን አንብቦ የቃል ክፍሎች እንዴት እንደቀረቡ እና እነዴት አንደተዋቀሩ አይነታቸውን ከአገባባቸው ተነስተን መለየት የምንችልበት ማለት ነው፡፡

ክሂል 8፡ ለከባድ ቃላት ትርጉም መሰጠት (dertemining meaning of difficrt words)ከባድ ቃላት በምንባቡ መሰረት ያላቸውን አገባብ አውዳዊ ፍቺ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ፣ በማጥነቅና በማላላት መለየት መቻል ማለት ነው፡፡

ክሂል 9፡ ለቀላል ቃላት ትርጉም መስጠት (determining meanings of simple words) ለቀላል ቃላት ትርጉም መስጠት በተመሳሳይ፣ በተቃራኒ፣ በዘዬ፣ በማጥበቅና በማላላት በምንባቡ መሰረት መፍታት መቻል ማለት ነው፡፡

ክሂል 10፡ የአንቀፅ ሀይለ ቃልን መፈለግ (Determining where specific information found) ከምንባቡ ጽሑፍ ውስጥ ከየአንቀፆቹ ሀይል ቃሎችን መፈለግ ምንባቡን አንብበን

ፍሬ ሀሳቡን መረዳት፣ ተረድተን ሀይለ ቃል በየትኛው ቦታ እንደሚገኝ መለየትና መረዳት እንዳለብን ይገልፃል፡፡

ክሂል 11፡ የንባብ ብለሀቱን መረዳት (Determing the tone purpose or course

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ነገሮችን በመከተል ቢያነቡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆን እንረዳለን፡፡

## 2.1.7.2 የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች

ፍትፍቴ (2010) ተፈታኙየአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው ወይም የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤቱ ከሚጠበቀው በታች ነው ለማለት በፈተና ውጤት ደረጃ ሊሰጠው እንዲሚገባ ገልፃለች፡፡ Hugles (1989)በመርህ ደረጃ ተፈታኞች ፈተና የቀርበውን ፅሁፉ ተረድተውታልለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ነገር ግን የሠው ልጅ በፅሁፍ የቀረቡ መልዕክቶችን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት ስለሚገነዘብ ይህ ብቃት ሁልጊዜ ይኖራል ማለት አይቻልም፡፡ በማለት ገልጿል፡፡ ስለሆነም የአንባቦ መረዳት ተፈታኞች 80 ከ100 በላይ ውጤትካስመዘገቡ ፅሁፍን ተረድተውታል ለማለት ያስችላል ሲል ያብራራል ፡፡

Nutan (1982) እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈታኞች 70 ከ100 ውጤት ካመጡ ፅሁፉን ተረድተውታል ለማለት ያስቻላል፡፡ በተጨማሪ ማስተዋል(1989) ምሁራንን በመጥቀስ የአንባቦ መረዳት ችሎታ ደረጃን እንደሚከተለው እንደገፀው ፍትፍቴ (2010) ጠቅሳለች፡፡በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በተለመደው ፍጥነቱ በማንብ የሚሰራው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና 70% ሊያገኝ ይገበዋል፡፡ ውጤቱ70% በላይ ከሆነ ጥሩ ችሎታ አለው ሊባል ይችላል፡፡

የተፈታኙ ውጤት ከ50% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡Narhyanas wamy(1775) የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ተገናዝቦ መታየት እንደሚገባውና አንባቢዎች አንድን ፅሁፍ በአማክኝ የንባብ ፍጥነት አንብበው 70 ከ 100 ውጤት ካመጡ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መሰረት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ይኸውም አንባቢዎች ከ 10 ከታረመ ፈተና ከ5 በታች ውጤት ያመጡ በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ5-6 ውጤት ያስመዘገቡ መጠነኛ ነገር ግን በቂ ያልሆነ ፣ 7 ያገኙ ጥሩ እና ከ 8-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው በማለት እንደሚከፋፈል አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከሙራኑ እና ከተመራማሪዋ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የንብቦ መረዳት ችሎታ የሚለካው በተማሪ ውጤት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ ከግማሽ በላይ

ከአመጡ ተረድተውታል ወይም ሀሣቡን ተገንዝበዉታል ፤ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ጥሩነው ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን ፡፡

## 2.1.8 የአንብቦ መረዳት መስፈርቶች

አደይ (2012) የምሁራኑን አገላለፅ መሰረት አድርጋ እንደሚከተለው ገልፃለች መገንዘብ ና መረዳት Applegate.et al(2009)አንብቦ መረዳት ማለት አንድን ፅሁፍ በፍጥነት ፣በትክክልና ግልፅ በሆነ ሁኔታ በማንበብ የፅሁፉን ይዘትና መልዕክት ትርጉማ ባለው መንገድ መገንዘብና መረዳት ማለት ነው፡፡ስለዚህ ማንበብ ሂደት መዳበር የመምህራን ትምህርት አሰጣጥ ወሣኝ ሚና እንዳለው በመግለፅ የማንበብ ትምህርት ንድፍ ሀሣቦችና መርሆች ጋር የተጣጣመ መሆን እንዳለበት አብራርቷል፡፡

Brown (1996) እንደገለፀው በማንበብ ላይ ተፅኖ የሚያደርሱበት ግላዊ ተላውጦዎች መኖራቸውን አሳይቷል፡፡እነዚህም ጭንቀት፣ የተነሻሽነት ሁኔታ፣ ትኩረት፣ በራስ የመተማመንና የማንበብ አላማ መሆናቸውን በመግለፅ የማንበብ ክሂል ማስተማር እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከግምት ያስገባ መሆን እንዳለበት ይገላፃል፡፡ ስለዚህ አንድ መምህር ሲያስተምር ከተማሪዎቹ ወቅታዊ ሁኔታ አኳያን በመነሳት መገንዘብና መረዳት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት ማለት ነው፡፡

***ሀ. ፊደላትን ከድምፅ ምልክታቸው ጋር ማዛመድ*** Erik (1998) ተማሪዎች ፊደላት ከድምፅ ምልክታቸው ጋር ማዛመድ የሚለምድበት እና ይህንኑ በንባብ ተግባራቸው ውስጥ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይሁንና ግን በፊደላት እና በድምፅ መሀል ያለውን መስተጋብር በአግባብ መግንዘብ ስለማይችሉ ፊደላትን እና ድምፆች ያላቸውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ለይተው መጠቀም የሚችሉ አይሆኑም፡፡ ነገር ግን በዚህ ደረጃ የአንድ ቃል ፊደላት የቃሉ ድምፅ መሆናቸን መለየት ይችላሉ፡፡

ለ. እይታErik (1998) እይታ ማለት ፊደላቱን፣መልክቱንና ድምጹን እንዲሁም በአረፍ ተነገር የሚኖረውን ትርጉማዊ ሚና ጨምሮ ቃላትን ከትውሰታ መሀደር ውስጥ በፍጥነት ለይቶ በማውጣት የትክክለኛነትና የፍጥነት ጉዳይ ከቃላት ምስረታ ይልቅ ወደ ትርጉም መሸጋገሩን የሚገልፅ ነው፡፡

**ሐ. የቃላት ልየታ/ ምስረታ**Tunner (2008) የቋንቋ ግንዛቤ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሰረት ናቸው ብሏል፡፡ አገላለጹም ተማሪዎች ከንባብ ተግባራቸው ትርጉም የማግኘት ችሎታ ይወሰናል፡፡ ሁለቱም የቃላት ምስረታ እና የቋንቋ ግንዛቤ ችሎታዎች አንብቦ ለመረዳት በእጅጉ እኩል ጠቃሚዎች መሆናቸውን አስቀምጠዋል፡፡

### 2.1.9 የመማር ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ

ለመማር ማወቅ ያስፈልጋል። ለማወቅ ደግሞ ማሰብ ትልቅ እዉቀትና አስተሳሰብ ያለዉ ሰዉ ደግሞ አንባቢ ነዉ። ቀጥሎም ለመማር እና ለማወቅ ማንበብ ትልቅ ክሂል መሆኑን እና አላማን ለማሳካት ንባብ መፈለግ እንዳለብን ይገልጻል። ለፈተና ዉጤት ደግሞ ማንበብ ትልቅ ቦታ አለዉ። ለማንበብም ሆነ ጥሩ ዉጤት ለማምጣት ደግሞ ተነሳሽነት አስፈላጊ መሆኑን እንረዳለን። christopor(2000) አንብቦ የመረዳት ችሎታ የከበደንና የተወሳሰበን ነገር በትምህርት የምንናገኝበት ወይም ከመምህራን የምንረዳበት ክሂል መሆኑንገልጿል።

Planig (2006) ተነሳሽነት ያላቸዉ ተማሪዎች ቋንቋን ይሰሙታል፤ ከሰሙት ደግሞ ይናገሩታል፤ ከተናገሩት ደግሞ ይማሩታል፤ ከተማሩት ደግሞ ያነባሉ። በማለት የማናበብና የመማር ተነሳሽነትን ግንኙነት አስቀምጧል። አማረ(2011) ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያለዉ የቋንቋ ተማሪ ታላሚዉን ቋንቋ የሚማረዉ በተማረዉ ቋንቋ አንዳች ጥቅምን ፈልጎ ወይም ሌላ በስተጀርባዉ የሚገፋፋዉ ሀይል ኖሮት ሳይሆን ቋንቋዉን በመማሩ ከሚሰማዉ ዉስጣዊ እርካታ በመነሳት በግሉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን ለማሳካት ትኩረት የሚያደርግበት ነዉ በማለትገልጿል። ንባብ ማለት ተግባር (ተግባሮች) ሆኖ አንድ ሰው ምልክቶች፣ ፊደላትንና ምህፃረቃላትን ወደቃላት (ቶች) ፊደላትና ምፃረቃላትን ወደ ቃላት (ቶች) እና አረፍተ ነገር (ሮች) ቀያይሮ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ የሚረዳበትና የሚጠቀምበት ሂደት ነው። የራሱ የሆነ እይታ አለው።ግቡ በፅሁፍ የሰፈረውን በተገቢው መልኩ መረዳት መቻልእና ነገሮችን መገምገም መቻል፣ እንዲሁም ለአንድ ፍላጎት መጠቀም መቻል ይሆናል።

Grellent (1991) አንብቦ መረዳት ማለት አንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት መሰብሰብ መቻል ማለት ነው። በዚሁ ሂደት ውስጥ አንባቢው የሚፈልገፈውን መረጃ ብቻ እየመረጠ መያዝ እንዳለበት ያስረዳናል።በዚህም መሰረት የአሀድን መሰረታዊነት ተረድቶ ዝርዝሩን በብቃት መገንዘብ አለበት ማለት ነው።

Smith (1985) አንባቢው ቀድሞ ይዟቸው ለተነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ማለት ነው።ጥያቄ መጠየቅ የአንብቦ መረዳትባህሪው ነው። አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ካገኘ በአንባቢው እናበፀሀፊው መካከል ተግባቦት ይፈጠራል፤ ተግባቦት የሚፈጠው ደግሞመረዳት ሲኖር ነው።

ከሙሁራኑእንደምንረዳው አንብቦ መረዳትመልክትመቀበያ መሆኑን፣ጥያቄ የምንመልስበት፣ ከፀሀፊው ጋር የምንገናኝበት የምንፈልገውን መልዕክት የምናገኝበት፣ ስንፈልግም የምንዝናናበትና እውቀት የምንጨብጥበት መሆኑን እንገነዘባለን። ማንበብም ሆነ አንብቦ

መረዳት የሚገኘው ደግሞ  በትምህርት ብቻ ነው ትምህርቱን ለመማር ደግሞ ተነሳሽነት ያስፈልጋል፡፡

ለመማር ማወቁ ያስፈልጋል፤ ለማወቅ ደግሞ ማሰብ ትልቅ እዉቀትና አስተሳሰብ ያለዉ ሰዉ ደግሞ አንባቢ ነዉ፡፡ ቀጥሎም  ለመማር እና ለማወቅ ማንበብ ትልቅ ክሂል መሆኑን እና አላማን ለማሳካት ንባብ መፈለግ እንዳለብን ይገለጻል፡፡ ለፈተና ዉጤት ደግሞ ማንበብ ትልቅ ቦታ አለዉ፡፡ ለማንበብም ሆነ ጥሩ ዉጤት ለማምጣት ደግሞ ተነሳሽነት አስፈላጊ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ፀጋ ዘአብ (2006) የመማር ተነሳሽነት ትምህሩቱን ለማወቅ፣ ለመቀበል ያለው ተነሳሽነት ሲሆን አንብቦ መረዳት ደግሞ የንባብ ባህል፣ የንባብ ጠባይ፣እምነት፣እይታ እናየእውቀት ድምር ውጤት ነው፡፡ Shanani (2006) አንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ መረዳትና በሚገባ መጨበጥን እንደሆነ እና ከአውዳዊ ውጭ የሆኑ ፍቺዎችንም መረዳትን የሚያጠቃልል እንደሆነ ገልጿል፡፡

መሪነሽ (2004) ጉሪዝና ዉግፊልድን በመጥቀስ የማንበብ ተነሳሽነት ሲጨምር የአንብቦ መረዳት ውጤት ይጨምራል፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ የማንበብ ተነሳሽነት ያላቸው ከፍተኛ የማንበብ ውጤት ያላቸው ሲሆኑ በአንፃሩ ደግሞ ውጤታማ አንባቢዎች ለማንበብ ተነሳሽነት ያላቸው መሆናቸውን በጥናት ማረጋገጣቸውን ገልፃለች ፡፡

መማር  እና ማንበብ  ጠንካራ ግንኙነት አላቸው አንድ ሰው ለማንበብ መጀመሪያ መማር አለበት፤  ለመማር ደግሞ  ተነሳሽነት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለመማር ተነሳሽነት  ያላቸው ተማሪዎች ለማንበብና አንብቦ ለመረዳትም ጎበዞች ናቸው፡፡ለዚህም ማስረጃ ለትምህርታቸው ትኩረት የሚሰጡ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ለትምህርታቸው ትኩረት የማይሰጡ ተማሪዎች ደግሞ ዝቅተኛ  አንባቢ መሆናቸውን በማሳየት ለመማር እና ለማንበብ  ተነሳሽነት አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል፡፡

እንደምሁራኑ  ሃሳብ  ዝቅተኛውጤት  የሚያስመዘግቡ  ተማሪዎች  ምክንያት  የግል ተነሳሽነትና ማንበብ ፍላጎት  አለመኖር ምቹ ትምህርት እንዳይሰጥ  ያደርጋል፡፡

## 2.2 ፅንሰ ሀሳባዊ ማህቀፍ

የቋንቋ ትምህርት አላማ  አራቱ የቋንቋ  ክህሎቶች ለማዳበር  በመሆኑ ከነዚህም  ውስጥ አንዱ አንብቦ መረዳት ነው፡፡አንብቦ መረዳት ባለፉት ምዕራፎች እንደተገለፀው ከማንበብ ባለፈ ነው፡፡ ይህም  አንብቦ መረዳት  ከማንበብ ባለፈ  መረዳት፣ መገንዘብ እና መልዕክት መቀበል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳትንም ሆነ ማንበብን ለማወቅመማር አስፈላጊ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ካልተማረ በስተቀር ማንበብ አይችልም፡፡ ማንበብ ካልቻለ

ደግሞ ከፀሀፊያን ጋር መግባባት አይችልም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የመማር ተነሳሽነት ካለና ከተማርን ማንብብም ሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ አንብቦ መረዳት ከተቻለ ደግሞ ጥሩ ውጤት በማምጣት ከክፍል ወደ ክፍል መሸጋገር ይቻላል፡፡ ለወደፊት አላማ ግብ መምታትም መሠረት ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የመማር ተነሳሽነት፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የወደፊት ግብ እርስ በእርስ የተቆራኙ እና የአንዱን መኖር ለሌላው ውጤት ማምጣት አስፈላጊ በመሆኑ የቋንቋ ትምህርት መሰረቶች ናቸው፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው እናያለን፡፡




## 2.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ዘሪቱ (2004) የጥናቱ አላማ አማርኛን በ2ኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ የሚል ሲሆን አፋቸውን በጋምኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎችላይ ሲሆን በተደረገው ጥናት በተነሳሽነት አይነቶችና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ጠቅሳለች፡፡ በውህዳዊ እና በውጫዊ ተነሳሽነት መካከል ተዛምዶ መኖሩን ገልፃላች፡፡

በተጨማሪም በተለዋዋጭ አይነቶች ተላውጠዎቹን በፆታ በመከፋፈል ባደረገቸው ስሌት በፆታ እና በውህደት፣ በፆታ እና በውጫዊ፣ በፆታ እና በጥቅማዊ ተነሳሽነት መካከል ጉልህ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ጠቁማለች፡፡ በተገኘው ግኝት እና ውጤትም የጋሞኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች በቡድን አማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት እንዳላቸው አረጋግጣለች፡፡ በፆታ በተደረገው የቲ- ቴስት ናሙና ትንተና የሴት ተማሪዎች አማርኛ የመማርምሆነ የትምህርት ውጤታቸው ተዛምዶ አንሶ መገኘቱን ገልፃለች፡፡

መሪነሽ (2004) የጥናቷ ዋና አላማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምራለች፡፡ በዚህም

የተማሪዎችን ተነሳሽነት በውስጣዊ እና ውጫዊ በፆታ ከፋፍላ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን መርምራለች። ውጤቱ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰናኛ ተሠልቶ የተገኘው ውጤት በውስጣዊ የማንበብ ተነሽነት ተዛምዶ አለማሳየቱን ገልፃለች። በአጠቃላይ ጥናቱ በቡድን የማንበብ ተነሳሽነት እንደላቸው ጠቁማለች።

ድንቅነህ (2011) የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብ ብልሀቶች አጠቃቀምና የማንበብ ተነሳሽነት ተዛምዶ ሲሆን ባካሔደው የፈተና ሙከራ ውጤት በነፃ ተላውጦዎቹ ባለው ዋጋ ትይዩ በጥገኛው ተላውጦ የሚገኙ ዋጋዎች መደበኛ ልይይት ተመሳሳይነትን ፈትሿል። በዚህም መሰረት በሁለቱ ተላውጦዎች ያለው ቀጥተኛ በብትን ግራፍ በመፈተሽ ተላውጦዎች ግንኙነት እንዳላቸው አስረድተዋል በግኝቱም የማህበረ ስሜታዊ የማንበብ እና ብለሃት አውነታዊ እና የላቀ የመተንበይ ድርሻ እንዳለው ገልጿል።

ፍትፍቴ (2013) ዋና አላማ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ንፅፅር ፆታ ተኮር ጥናት የሚል ሲሆን በጥናቱ ውጤቱም ባገኘቸው መረጃዎች የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከለኛ መሆኑን በወንድ እና በሴት ተማሪዎች መካከል በተደረገው ንፅፅር ደግሞ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የበለጠ ውጤት ማምጣታቸውን ገልፃለች።

እተኔሽ (2010) ዋና አላማዋ የተማሪዎች የማንበብ ልማድ እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ የማንበብ ልምድየአንብቦ መረዳት ችሎታን የማጉላት ትልቅ ሚና እንዳለው አይታለች።

አደይ (2011) የጥናቷ ዋና አላማ የአራተኛ ክፍል አፈፈት ተማሪዎች አቀላጥፈው ማንበብ እና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ የሚል ሲሆን ባገኘችው የጥናት ውጤት እንዳረጋገጠችው የተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበብ ዝቅተኛ መሆኑን ገልፃለች። በነጠላ የናሙና ፍተሻ እንደገፀችውም የተማሪዎች በትክክል የማንበብ አማካይ ዋጋ የጉልህነት ደረጃ አንሶ መታየቱን አስረድታለች። መረጃውን በፒርሰን የተዛምዶ ማሳያ ቀመር ተሠልቶ የአቀላጥፎ ማንበበ እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ግንኙነት እንዳላቸው ገልፃለች።

በአጠቃላይ የጥናቱ ይዘት በአንድም በሌላም መንገድ ይሁን ተነሳሽነት የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ጥናቶች ለዚህ ጥናት እንደመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ። ተመራማሪዎቹ ይዘውት እንደየተነሱበት አላማ እና መሪ ጥያቄዎች መረጃዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅመው የተለያዩ ግኝቶች ላይ ደርሰዋል ። አደይ በአቀላጥፎ የማንበብ እና አንብቦ መረዳት መካከል ዝምድና አለመኖሩን ስትገለፅ መሪነሽም በውስጣዊ ተነሳሽነት በአንብቦ መረዳት መካከል ጉልህ ዝምድና አለመኖሩን ባገኘችው ውጤት ገልፃለች ። ድንቅነህ ደግሞ  የማንበብ አመለካከት አንብቦ መረዳት ግንኙነት እንደላቸው አሳይቷ። ዘሪቱ

በተነሳሽነት አይነቶችና በአማርኛ ቋንቋ  መካከል አለመኖሩን ጠቅሳ ተማሪዎች በቡድን የመማር ተነሳሽነት እንደላቸው አመልክታለች፡፡ ፍትፍቴ ፣መሪነሽ ፣ዘሪቱ ባገኙት መረጃ በፆታ መካከል ያለውን ልዩነት መርምረው ሴቶች ከወንዶች በበለጠ ተነሳሽነት  እንዳላቸውና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የተሻለ እንደሆኑ አመልክተዋል ፡፡ መሪነሽም ልክ እንደዘሪቱ ተማሪዎች በቡድን የማንበብ ስሜት እንዳለቸው ገልፃለች፡፡

ተስፋዬ (2014) የጥናቱ ዋና አላማ በሁሩሙ እና በሶንጣ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ የሚል ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ የጽሑፍ መጠይቅና የችሎታ መለኪያ ፈተና ናቸው፡፡ የጥናት አይነቱ መጠናዊ ሲሆን የጥናቱ ንድፍ ተዛምዶአዊ ስልትን የተከተለ ነው፡፡ በመሆኑም የተስፋዬ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ በጥናቱ ስነ- ዘዴ በአስረኛ ክፍል ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው የተነሳሽነት አይነቶችን በአራቱም ተለውጦዎች ማየቱ ሁለት ትምህርት ቤቶችን ወስዶ ማወዳደሩ እንዲሁም የትምህርት ውጤትን ማንሳቱ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ይህ ጥናትም የአንበብቦ መረዳት ችሎታ በማንሳቱ ከተስፋዬ ጥናት ይለያል፡፡ ተስፋዬ በጥናት ውጤት የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት አይነቶች እና በአንብቦ መረዳት መካከል ተዛምዶ እንዳለ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ አወንታዊ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ፆታን በጣልቃ ገብነት በማየት ሴቶች በጥቅማዊ ተነሳሽነት ከወዶች የበለጠ ተነሳሽነት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

በቀለ(2009) የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የማነሳሻ ስልት አተገባበር ትንተና በሚል ርዕስ የሰራ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ምልከታ፣ ቃለ መጠየቅ እና የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ የጥናቱን ዋና ትኩረት ከግብ ለማድረስ አገልግት ላይ ውለዋል፡፡ ትኩረት ያደረገው ናሙና በሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ለየትኞቹ የመነሳሻ ስልቶች እንደሚጠቀሙበት እንዴት እንደተገበሩአቸው ያጠና ሲሆን ባገኘው ውጤት መምህራን የተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲጨምር የተለያዩ ዘዴዎችን መፍጠር እንዳለባቸው አስቀምጧል፡፡  ይህም ቀልዶችን፣ የተለያዩ የስነ- ፅሁፍ ውጤቶች በተለያዩ እና ሳቢ በሆነ መንገድ ማቅረብ እንዳለባቸው ያሳየ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ተነሳሽነት በማንሳቱ ሲሆን ልዩ የሚያደርገው ትንተና መሆኑንና ተዛምዶን አለመከተሉ አንብቦ መረዳት አለማካተቱ ነው፡፡

Knoll(2000) ዋና አላማው የተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ የሚል ሲሆን አንደ ጥናቱ የሚመለከታቸው አካላት ወላጆች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እና ሌሎች አካላትም ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ብሏል፡፡ አንብቦ መረዳት እና ተነሳሽነትም ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳላቸው መረጃዎቹን በመጥቀስ ገልጿል፡፡ ይህም መጀመሪያ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት በመማር ማስተማር ሂደት በትክክለኛ መመሪያ መሆን እንዳለባቸው ገልጿል፡፡ ባገኘው መረጃም ዝቅተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ አንባቢ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በማንኛውም የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ለአላማቸው ግብ መምታት በከፍተኛ መነሳሳት ማንበብ እንዳለባቸው የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

Kissau በ2ኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተነሳሽነት በፆታ ያለውን ልዩነት ያየ ሲሆን በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ተሳታፍዎቹ 490 ሲሆኑ ዕድሜያቸው ከ13-18 ሲሆን ከነዚህ ተማሪዎች መካከል 8 ተማሪዎች 4 ወንድ 4ሴት ተማሪዎች በመውሰድ በተደረገው የጥያቄ ውድድር ስምንቱም ተማሪዎች ማለፋአቸውን ገልጿል፡፡ በተገኘው ማስረጃም እኩል ተሳታፊ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡

Hassan and Ramli አላማ አድርገው የተነሱት በሴት እና በወንድ ተማሪዎች መካከል ያለን ተነሳሽነት ሲሆን 2ኛ ቋንቋቸው ስፓኒሽኛ ቋንቋ የሆነ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የተሳታፊዎቹ ብዛት 448 በተገኘው መረጃ በሴት ተማሪዎች እናበወንድ ተማሪዎች መካከል የተለያየ ተነሳሽነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ተማሪዎች የየራሳቸው የሆነ የተነሳሽነት ተሰጥኦ እንዳላቸውም ጠቁሟል፡፡ Henry A. (2011) አላማ አድረጎ የተነሳው የተማሪዎች ተነሳሽነት በፆታ ያለውን ልዩነት ከፋፍሎ ሲሆን በሴት እና በወንድ ተማሪዎች ወጥ የሆነ ተነሳሽነት አንዳላቸው ጠቁሟል፡፡

Ahmdi (2013) ዋናአላማው የማንበብ ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ የሚል ሲሆን አራቱንም የተነሳሽነት አይቶች በዝርዝር በማየት እና የምሁራኑን ሀሳብ በማንሳት ገልጿል፡፡ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሞዴሎችንም አንስቷል፡፡ የአንብቦ መረዳትእና የማንበብ ተነሳሽነት ከፍተኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳላቸውም አስቀጧል፡፡ በጥናቱም የማንበብ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች አወንታዊ አመለካከት እና ለችግሮቻቸው መፍትሔ በመስጠት ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

ተመራማሪዎቹ ተነሳሽነትን በተለያየ መንገድ ያንሱ እንጅ ፆታን በጣልቃ ገብነት ማየታቸውና በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ መስራታቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ሁሉም እንደየተነሱበት አላማ እና መመለስ የፈለጉአቸውን ነገሮች ለመርመር የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችንና መተንተኛ ዘዴዎችን እንዲሁም የመፍትሔ ሀሳቦችን አስቀምጣዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች ከዚህ በላይ እንደቀረበው ይህን ጥናት በከፊል የሚዛመዱ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ዘሪቱ (2004) የተማሪዎች የመማር ተነሣሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ የመረመረች ሲሆን በተነሣሽነት አይነቶች እና በትምህርት ውጤት መካከል አወንታዊ ዝምድና መኖሩን ስታረጋግጥ በተነሳሽነት አይናቶች እና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል አወንታዶ ተዛምዶ አለመኖሩን አረጋግጣለች፡፡ በተጨማሪም የሁለት ክፍል ደረጃዎች መካከል ያለውን ተነሣሽነት በማየት ፆታን እንደ ጣልቃ ገብነት በመጠቀም ያለውን ዝምድና ፈትሻለች፡፡ ይህ ጥናትም የትምህርት ውጤትን አጠቃላይ የማያይ ሲሆን አንብቦ መረዳትን ብቻ ነጥሎ የሚመረምር በመሆኑ ከዘሪቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ መሪነሽ (2004) የተማሪዎቹን የማንበብ ተነሣሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላውን ተዛምዶ ፆታን ጣልቃ ገብ አድርጋ በተነሣሽነት አይነቶች በውስጣዊ እና በውጫዊ ተነሣሽነት የፈተሸች ሲሆን የተማሪዎች የማንበብ ተነሣሽነት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ ጉልህ ድርሻ እንዳለው በጥናት ውጤቷ አረጋግጣለች፡፡ ይህ ጥናትም የማንበብ ተነሣሽነትን ባለማየቱ ከመሪነሽ ጥናት ልዩ ያደርገዋል፡፡ በቀለ (2009) የተማሪዎችን ተነሣሽነት የመምህራን የአተገባበር ሚነ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚወስድ በጥናቱ ሲያረጋግጥ ይህ ጥናትም እንደ መፍትሔ ሀሣብ የእሱን ጥናት እንደተዛማጅ ቅጥት መጠቀሙ አጋዥ ነው፡፡

Knoll (2000) ለተማሪዎች አለማ ግብ መምታት ዋናው ጉዳይ እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ዝቅተኛ ተነሣሽነት ያለቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ውጤት እንዳለቸው በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጥናቶች በማስረጃ እንዳረጋገጡት ለመማርም ሆነ አንብቦ ለመረዳት ወይም የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሣካት ተነሣሽነት ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ በተለያዩ መንገድ ገልፀዋል፡፡ ይህ ጥናተም ለጥናቱ ውጤት መሣከት እና ለማስረጃነት የነዚህ ጥናቶች ተጋሪ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍ እና አካሄድ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥናቱ የተከተለው ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የተከተለውን የንድፍ አይነት የትምህርት ቤት እና የተማሪዎች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይትና የችሎታ መለኪያ ፈተና የመረጃ አተናተን ዘዴ በዝርዝር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት አብይ አላማበሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም መጠናዊ የምርምር አይነትን ተከትሏል፡፡ የጥናቱን ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስም ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ አጥኚዋ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን የተከተለችበት ምክንያት በተምሪዎቹ የመማር ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን በሁሩሙ ወረዳ ሁሩሙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ ፡፡ በሁሩሙ ሁለተኛ ትምህርት በ 2014 ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ቦታዉ የተመረጠበት ምክንያት በአመቺ የንሞና ዘዴ ሲሆን የአጥኚዋ የስራ ቦታ በመሆኑ ተማሪዎቹን በቅርበት ለመከታታል እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ የርዕሰ መምህሩን እና የሌሎች መምህራን ድጋፍ ለማግኘት አመቺ በመሆኑ ነዉ፡፡ በተጨማሪም አስተዳደራዊ እርዳታዎችና የሙያ እገዛዎች እና ጥያቄዎችን ለመገምገምና ለመፈተን እንዲያመች በመታሰቡ ነዉ፡፡

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ተጠኚዎቹ በዚሁ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት በአላማ ተኮር የንሞና

ዘዴ ነዉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ወደ 11ኛ ክፍል ሲያልፉ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ እና ከሁለተኛ ቋንቋቸዉ አንዱን መርጠዉ የሚማሩ በመሆናቸዉ ከወዲሁ ያላቸዉን ተነሳሽነት ለማወቅ በመታሰቡ ነዉ፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ያልተመረጡበት ምክንያት አማርኛ ቋንቋን ከአፍ ፈት ተማሪዎች ጋር ለመማር የመጀመሪያ ጊዚያቸዉ ስለሆነ መረጃ ለመስጠት ይቸገራሉ በሚል ነዉ፡፡ የ11ኛ ክፍል እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ያልተካተቱበት ምክንያት አማርኛ ቋንቋን መርጠዉ የሚማሩ ተማሪዎች ዉስን በመሆናቸዉ ነዉ፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ9 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተመድበዋል፤ በነዚህ ክፍሎች ውስጥም 485 ተማሪዎች ሲገኙ ወንድ 232 ሴት 252 ተማሪዎች በጾታ ተለይተው ተመዝግበዋል፡፡ በየክፍሉም በአማካኝ ከ55-60 ተማሪዎች ይገኛሉ ከነዚህ ተማሪዎች መካከል 20 ፐርሰንቱ በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ ሌሎች ተማሪዎችን እንዲወክሉ ተመርጠዋል፡፡ ይህም ሴት60 ወንድ37 በድምሩ 97 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡

ይህ የናሙና አመራረጥ ሂደት ሳይንሳዊ ዘዴን ለመከተል ያለዉ (2011)ን መሰረት በማድረግ እድል የደረሰዉ ወይም እጣዉ የወጣለት ተማሪ የጥናቱ ተሳታፊ ሆኗል፡፡ ይህ ቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ እያንዳንዱ የጥናት አካላይ እኩል እድል አለው፡፡ አንዱ ከሌላዉ አይበልጥም ወይም አያንስም፡፡ በዚህ መሰረትም በእያንዳንዱ ክፍል ባሉ ተማሪዎች ልክ ቅርፅ እና መጠናቸዉ እኩል የሆኑ ወረቀቶች አንድ እና ዜሮ ቁጥሮች ተፅፎባቸዉ ተጠቅልለዉ ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ የመማርያ ክፍሎች አስራ አንድ አስራ አንድ ተማሪዎች የቀሩት ሁለት የመማሪያ ክፍሎች አስር አስር ተማሪዎች እጣዉን አንስተዋል፡፡ በመቀጠልም አንዳንድ ቁጥር ያነሱ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ዜሮ ያነሱት ሳይሳተፉ ቀርተዋል፡፡ በዚህ የእድል ሰጪ ንሞና የተሳተፉ ተማሪዎች 97 ማለትም 20% ሲሆኑ ቁጥር የሚመጣዉ አጠቃላይ ተማሪዎች 97×100%÷485 = 0.2×100=20% ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ 0.2 የመመረጥ እድል አለዉ ማለት ነዉ፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስና መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ዉለዋል ፡፡ እነሱም የመማር ተነሳሽነትን የሚያሳይ የጽሁፍ መጠይቅና የአንብቦ መረዳትችሎታን የሚያሳይ ፈተና ናቸዉ ፡፡ በተገኙት መረጃ ምንጮች አማካኝነት ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ተሰጥቶበታል፡፡

## 3.4.1. የጽሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ የተመጠረበት ምክንያት የተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሣሽነት መጠንን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት በመታሰቡ ነው፡፡ መጠይቁ በአጠቃላይ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸውን ተነሣሽነት ለመላካት ነው፡፡ በመጠይቁ የተካቱት መጠይቶች በሀገር ውስጥ ጥናቶች የድንቅነህ (2011) የመሪነሽ (2004) በአቀራረብ ስልቶች መነሻ በማድረግ በአጥኚዋ ተሻሽለው ይበልጥ ለአላማው መሣካት የሚሆነውን በመጠቀም ነው፡፡በመሆኑም በውስጣዊ እና በውጫዊ የመማር ተነሣሽነት እንዲከተቱ ተደርጓል፡፡ ውስጣዊ የመማር ተነሣሽነትን የሚመለከቱ 22 ጥያቄዎች 1፣4፣5፣7፣8፣9፣11፣12፣13፣14፣15፣16፣17፣20፣21፣22፣22፣24፣25፣29፣29፣30 ሲሆኑ የውጫዊ ተነሣሽነትን የሚመለከቱ8 ጥያቄዎች 3፣4፣6፣18፣19፣23፣26፣28 ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በአሉታ መልክ የቀረቡ በመሆናቸው በግልብጥ ኮድ በሰንጠረዥ መልክ ተመዝግበዋል፡፡ ጥያቄዎቹ የቅረቡት ከዘሪቱ፣ ከድንቅነህ እና ከመሪነሽ ማሻሻያ ተደርጎባቸው ባለ አምስት አማራጭ ሆነው በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም 5 በጣም እስማማለሁ 4 እስማማለው 3 በመጠኑ እስማማለሁ 2 አልስማማም 1 ፈፅሞ አልስማማም በሚሉ ትእዛዞች ቀርበዋል፡፡

የተዘጋጁት ጥያቄዎች በጥናቱ አማካሪና በትምህርት ክፍሉ መምህራን ተገምግመው የማስተካከያ ሀሣብ በመቀበል እንደገና ተፅፈዋል፡፡ ግልፀኝነት የጎደላቸውና አሻሚነት ያላቸው ቃላትና ሀረጋት ተስተካክለዋል፡፡ በመጨረሻም የመጠይቁ ትክክለኛነት ማረጋገጫ አልፋ ክሮባት ከ 0.67 በላይ መሆኑ ተረጋግጦ ለጥናቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

መረጃውን ለማሰባሰብ የትምህርት ቤቱን የአስተዳደር ሰራተኞች በማስፈቀድ፣ መምራኖችንና ተፈታኝ ተማሪዎችን በማስተባበር በትርፍ የመማሪያ ክፍል መጠይቁ ተሰራጭቷል፡፡ መጠይቁን እንዴት መሙላት እንዳለባቸው እና የየራሳቸውን ትክክለኛ ስሜት መግለፅ እንዳለባቸው ባጥኚዋና መጠይቁን በሚያስሞሉ መምህራን ማብራርያ ተሰጥቶ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በመቀጠልም ለጥናቱ አተናተን እንዲያመቺ ኮድ ተሰጥቷል፡፡

## 3.4.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና

የአንብቦ መረዳት ፈተናው የተዘጋጀው በአጥኝዋ ሲሆን የተማሪዎቹን አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት መረጃ ለማግኘት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተናው መሰረት ያደረገው የመማሪያ መጽሐፍና የመረሃ ትምህርቱን ይዘት መሰረት ያደረገ የተለመደውን

የፈተና አወጣጥ ስልት መሰረት ያደረገ ነው። ይህም የፈተናው ጥያቄዎች በተማሪዎቹ ችሎታ፣ እድሜና የክፍል ደረጃ መሰረት ከልብወለዶችና ኢ ልብወለዶች የስነፅሁፍ ይዘት ያላቸው ይዘቶች ተዘጋጅተዋል። በዚህም የጥያቄዎች ግልፀኚነት፣ አሻሚነት፣ የስዋሰውና የስርአተ ነጥቦች ግድፈት በጥናቱ አማካሪና በትምህርት ክፍሉ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶበት እንደገና ተፅፏል።

የቀረቡት ምንባቦች አራት ሲሆኑ የእያንዳዳቸው የተለያዩ ጥያቄዎች አላቸው። በመቀጠል የትምህርት ቤቱን የአስተዳደር ሰራተኞች በማስፈቀድና የትምህርት ክፍሉን በማስተባበር በትርፍ የመማርያ ክፍል ተፈትነዋል። ፈተናውን በመጠይቁ መሰረት ኮድ ተፅፎበት ተማሪዎቹ እንዳይለዋወጡ ፈተናው ተሰራጭቷል። የተገኘው ውጤትም በትምህርት ክፍሉ መምህራን ታርሞ ወደ 100% ተለውጦ ተመዝግቧል።

## 3.5 የመረጃ አተናተን

የጥናቱ ተሳታፊዎች ከጽሑፍ መጠይቅና ከችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኙ መረጃዎች መልሶቻቸው በትክክል መሞላታቸው ከትንታኔ በፊት ተረጋግጧል። መረጃው በኤስ.ፒ ኤስ.ኤስ 21 የስታትክስ የመተንተኛ ፕሮግራም ለትንተና እንዲያመች ሆኖ በኮምፒውተርተመዝግቧል። ወደ ትንታኔ ከመግባቱ በፊትም የተሞላው መረጃ ትክክል መሆኑ ተረጋግጣል። ቀጥሎም በአልፋ ሌብልፒ = 0.05 ተሰልቷል።

የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ለማወቅ በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በነጠላ የናሙና ፍተሻተሰልቷል። የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት በውስጣዊና በውጫዊ ተነሳሽነት የውጤት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በጥንድ ናሙና ቲ.ቴስ ተተንትኗል። ከዚህ በመቀጠልም በመማር ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ተሰልቷል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና እና  የውጤት ማብራሪያ

